የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

# የክራውድ ፈንዲንግ ረቂቅ መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር ......../2019

**ማውጫ**

**መግቢያ**......3
ምዕራፍ አንድ ፤ ጠቅላላ ድንጋጌዎች......4
1. አጭር ርዕስ......4
2. ትርጓሜ......4
3. የተፈጻሚነት ወሰን......6
ምዕራፍ ሁለት ፤ ገንዘብ አሰባሳቢዎችና ኢንቨስተሮች......6
ክፍል 1፤ ገንዘብ አሰባሳቢዎች......6
4. ብቁ ገንዘብ አሰባሳቢዎች......6
5. ብቁ ያልሆኑ ገንዘብ አሰባሳቢዎች......7
6. በክራውድ ፈንዲንግ መድረክ የመመዝገብ ግዴታ......7
7. የምዝገባ መስፈርቶች......7
8. ገንዘብ የማሰባሰብ ጣሪያ......8
ክፍል 2፤ ኢንቨስተሮች......8
9. ብቁ ኢንቨስተሮች......8
10. የኢንቨስትመንት ገደቦች......8
11. የኢንቨስተር ምዝገባ......9
ምዕራፍ ሦስት ፤ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ ግዴታዎች......9
12. አጠቃላይ ግዴታ......9
13. የተገቢነት ቁመና ጥናት......10
14. ገንዘብ አሰባሳቢዎችን መመዝገብ......11
15. በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ይሁንታ......12
16. ኢንቨስተሮችን የመመዝገብ ግዴታዎች......12
17. ስጋትን ይፋ የማድረግ ግዴታዎች......13
18. የስጋት ማረጋገጫ ቅጽ......13
19. የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ በአቅርቦት ጊዜ ውስጥ ያሉበት ግዴታዎች......14
20. የመረጃ ጥበቃና ግላዊነት......15
21. የጥቅም ግጭት አፈታት......15
22. የተፈቀደ ድጋፍ አገልግሎት......16
23. የቅሬታ አያያዝ......16

24. የመዝገብ አያያዝ ግዴታዎች......17
25. ቀጣይነት ያለው ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ......17
ምዕራፍ አራት ፤ የክራውድ ፈንዲንግ ግብይት......18
26. የተፈቀዱ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች......18
27. የተከለከሉ ሰነደ ሙዓለንዋዮች እና ሰነዶች......19
28. ከሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ ነፃ መሆን......19
29. የሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱን ይፋ ማድረግ......19
30. የአቅርቦት  ክፍያዎች......19
31. የአደራ ዝግ የባንክ ሒሳብ......20
ምዕራፍ አምስት፡ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ማቅረቢያ ሰነድ ውስጥ መካተት ያለባቸው ዝቅተኛ ይፋ የማድረግ መስፈርቶች......20
32. የሽያጭ ማቅረቢያ ሰነድ ይዘቶች......20
33. በሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱ ላይ የሚደረጉ ወሳኝ ለውጦች......23
ምዕራፍ ስድስት ፤ የሽያጭ አቅርቦት ሂደትና ሥነ-ምግባር......23
34. በነባር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ የተጣለ የዝውውር ገደብ......23
35. የአቅርቦት ጊዜ......24
36. የተደነገገው ዝቅተኛ የገንዘብ መጠን ገደብ......24
37. በገንዘብ አሰባሳቢው የሚወጣ ማስታወቂያ......24
38. በክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ የሚወጣ ማስታወቂያ......25
39. በሽያጭ አቅርቦት ገጽ ላይ የሚቀመጡ ማስታወቂያዎች......26
40. የኢንቨስተሮች ኢንቨስትመንትን የመሰረዝ መብት......26
41. የሽያጭ አቅርቦትን ማገድ ወይም መሰረዝ......26
42. በገንዘብ አሰባሳቢው በፈቃደኝነት የሚደረግ መሰረዝ......27
43. ሽያጭን የማገድ ወይም የመሰረዝ ውጤት......27
44. ከመሰረዝ በኋላ በሚቀርቡ ተከታይ የሽያጭ አቅርቦቶች ላይ የሚጣል ገደብ......28
45.  የድልድል ሂደት......28
46. የድልድል ሪፖርት......29
47. ከአደራ ዝግ የባንክ ሒሳብ ገንዘብ ስለመልቀቅ......29
48. ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ስለ ማውጣት......30
49.  ለክራውድ ፈንዲንግ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የግብይት አደረጃጀት......30
ምዕራፍ ሰባት ፤ መረጃን በቀጣይነት ይፋ የማድረግ ግዴታዎች......31
50. መስፈርቶች......31
51. የሽያጭ ማቅረቢያና ቀጣይነት ያላቸው የመረጃ ይፋ ማድረጊያ ሰነዶች ተደራሽነት......32
52.መረጃ የማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳ......32

ምዕራፍ ስምንት ፤ አስተዳደራዊ እርምጃዎችና ቅጣቶች..........32
53. ያለ ፈቃድ የሚከናወኑ የክራውድ ፈንዲንግ ተግባራት..........32
54. የማጭበርበር፣ የሸፍጥ ወይም አሳሳች ተግባር..........32
55. ከገንዘብ አሰባሳቢ ብቁነትና ምዝገባ ጋር የተያያዙ ጥሰቶች..........32
56. የገንዘብ ማሰባሰብ ላይ የተቀመጡ ጣሪያዎችን ማለፍ..........32
57. የተሳሳተ አቀራረብና የተከለከለ ማስታወቂያ..........32
58. ወሳኝ ለውጥን ወይም ቀጣይነት ያላቸውን መረጃ ይፋ የማድረግ ግዴታዎችን አለመወጣት..........32
59. የተገቢነት ቁመና ጥናት አለማካሄድ..........32
60. ስጋትን ይፋ አለማድረግና የማስጠንቀቂያ መግለጫ አለማሳየት..........32
61. የስጋት ማረጋገጫ ቅጽ አለመቀበል..........32
62. በኢንቨስተሮች የሚፈጸሙ ጥሰቶች..........32
63. ሌሎች ጥሰቶች..........32
64. ባለሥልጣኑ ምርመራ የማካሄድ ስልጣን..........32
ምዕራፍ ዘጠኝ ፤ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች..........32
65. ተጨማሪ መረጃ እና የተገቢነት ቁመና መስፈርቶች..........32
66. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች..........32
67. መመሪያው የሚጸናበት ቀን..........32

# መግቢያ

አካታች፣ ግልጽ እና ውጤታማ የካፒታል ገበያ ማሳደግ በኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገትንና የግሉን ዘርፍ ልማት ለማፋጠን ቁልፍ ምሰሶ በመሆኑ፤

ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች በአጠቃላይ የኢኮኖሚ ልማት ውስጥ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ በመሆናቸው፣ ለእነሱ የካፒታል ገበያን ተደራሽነት ማመቻቸት ካፒታል ለማሰባሰብና ዕድገታቸውን እና ልማታቸውን ለመደገፍ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ኢንቨስትመንት ክራውድ ፈንዲንግ በኢትዮጵያ ውስጥ ላሉ ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች እና ስታርትአፖች አማራጭ የፋይናንስ ማግኛ ዘዴዎችን የሚያቀርብ በመሆኑ፤

የክራውድ ፈንዲንግ የሕግ እና የተቋም ማዕቀፍ ማዘጋጀት ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች ካፒታል ማሰባሰቢያ ተአማኒነት እና ስኬታማነት የሚያረጋግጥ በመሆኑ እና የሀገር ውስጥ ቁጠባን ስርአት ባለው መልኩ ወደ አምራች ኢንቨስትመንት ለማሰባሰብ የሚያግዝ በመሆኑ፤

ስለሆነም ባለሥልጣኑ በካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 አንቀጽ 55፣ 75 እና 108 መሠረት ይህንን የክራውድ ፈንዲንግ መመሪያ አውጥቷል።

## ምዕራፍ አንድ ፤ ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ *መመሪያ* "የክራውድ *ፈንዲንግ መመሪያ* ቁጥር ___/2019" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ *መመሪያ* ውስጥ፡-

1/ "**አዋጅ**" ማለት የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 ነው።

2/ **"ባለሥልጣን"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 3 (1) *መሠረት* የተቋቋመው የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ነው።

3/ **"የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2(7) ሥር የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል።

4/ **"የማስጠንቀቂያ መግለጫ"** ማለት በክራውድ *ፈንዲንግ* አገናኝ የሚቀርብና ኢንቨስተሮችን የሚያስጠነቅቅ እንዲሁም የሚመክር አስገዳጅ የስጋት መግለጫ ሆኖ የሚከተሉትን የሚያመላክት ነው፡-

ሀ) በኦንላይን የክራውድ *ፈንዲንግ* መድረክ አማካኝነት ኢንቨስት ማድረግ ስጋት ያለበት መሆኑንና በመድረኩ በኩል ገንዘብ ለማሰባሰብ የሚፈልጉ ገንዘብ አሰባሳቢዎች በአብዛኛው አዲስ ወይም ከፍተኛ ስጋት ያለባቸው ሥራዎችን የሚያካሄዱ መሆናቸውን፤

ለ) ኢንቨስተሮች በመደበኛው የንግድ እንቅስቃሴ ሂደት ውስጥ ኢንቨስት ያደረጉትን ገንዘብ ሊያጡ የሚችሉ መሆኑንና ይህንን ስጋት መሸከም የሚችሉ መሆን እንዳለባቸው፤

ሐ) ያለፉ ውጤቶች የወደፊት አፈጻጸምን የሚያመላክቱ አለመሆናቸውን፤

መ) ወደ ኢንቨስትመንት ከመግባታቸው በፊት የተሰጣቸውን መረጃ በሙሉ በጥንቃቄ ማንበብ፣ ጥያቄ መጠየቅና ገለልተኛ የፋይናንስ ምክር መጠየቅ አስፈላጊ መሆኑን፤ እና

ሠ) የኢንቨስተሮች የኢንቨስትመንት ጣሪያ በክራውድ *ፈንዲንግ* አገናኙ ክትትል የሚደረግበት መሆኑን።

5/ **"የንግድ ሕግ"** ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 ነው።

6/ **"ቁልፍ ኢንቨስተር"** ማለት በአንድ ገንዘብ አሰባሳቢ ውስጥ ጉልህ የባለቤትነት ድርሻ ለማግኘትና ለመያዝ የሚያስችል የፋይናንስ አቅም፣ ሙያዊ ብቃትና የረጅም ጊዜ ቁርጠኝነት ያለው እና በአብዛኛው

በምስረታው፣ በዕድገቱና በአስተዳደሩ ውስጥ እንደ ስትራቴጂክ አጋር የሚያገለግል ሰው ወይም የሰዎች ስብስብ ነው።

7/ **"ክራውድ ፈንዲንግ"** ማለት በፈቃድ አሰጣጥ መመሪያው አንቀጽ 2(17) ሥር የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል።

8/ **"የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ" ማለት** በፈቃድ አሰጣጥ መመሪያው ክፍል አሥር መሠረት በባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠውና የክራውድ ፈንዲንግ መድረክ የሚያንቀሳቅስ ሰው ነው።

9/ **"የክራውድ ፈንዲንግ መድረክ"** ማለት በፈቃድ አሰጣጥ መመሪያው አንቀጽ 2(18) ሥር የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል።

10/ **"የተገቢነት ቁመና ጥናት"** ማለት ከክራውድ ፈንዲንግ ሥራ ጋር በተያያዘ አንድን ሰው የሚመለከት መረጃ ትክክለኛነት፣ ሙሉነትና አስተማማኝነት ላይ ምክንያታዊ ምርመራ፣ ማረጋገጫና ግምገማ የማካሄድ ሂደት ነው።

11/ **"የአደራ ዝግ የባንክ ሒሳብ"** ማለት በሕዝብ ሽያጭ መመሪያው አንቀጽ 2(17) ሥር የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል።

12/ **"የፋይናንስ ተቋም"** ማለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው የንግድ ባንክ፣ የመድን ሰጭ ድርጅት፣ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ወይም ማንኛውም ሌላ የፋይናንስ አገልግሎት ሰጭ ተቋም ነው።

13/ **"ገንዘብ አሰባሳቢ"** ማለት ገንዘብ ለማሰባሰብ በማሰብ በክራውድ ፈንዲንግ መድረክ ላይ የሚስተናገድ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ የሚያወጣ ኩባንያ ነው።

14/ **"ተቋማዊ ኢንቨስተሮች"** ማለት በሕዝብ ሽያጭ መመሪያው አንቀጽ 2(23) ሥር የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል።

15/ **"ኢንቨስተር"** ማለት ለፋይናንስ ጥቅምና ከዚሁ ኢንቨስትመንት ጋር ለተያያዙ ሌሎች መብቶች ወይም ጥቅሞች ሲባል በክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ አማካኝነት ኢንቨስት ለማድረግ የሚፈልግ ወይም ኢንቨስት ያደረገ ማንኛውም ሰው ነው።

16/ **"ደንበኛህን ዕወቅ"** ማለት በፈቃድ አሰጣጥ መመሪያው አንቀጽ 2(36) ሥር የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል።

17/ **"የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ"** ማለት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 980/2016 ነው።

18/ **"ወሳኝ መረጃ"** ማለት በሕዝብ ሽያጭ መመሪያው አንቀጽ 2(31) ሥር የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል።

19/ **"የሽያጭ ማቅረቢያ ሰነድ"** ማለት አንድን ኢንቨስተር ከሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ጋር በተያያዘ የኢንቨስትመንት ውሳኔ ለማሳለፍ የሚረዳው አግባብነት ያለው መረጃ የያዘ ማንኛውም ሰነድ ነው።

20/ **"የሕዝብ ሽያጭ መመሪያ"** ማለት ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለሕዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ ቁጥር 1030/2017 ነው።

21/ **"ብቁ ኢንቨስተሮች"** ማለት በሕዝብ ሽያጭ መመሪያው አንቀጽ 2(46) ሥር የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል።

22/ **"መደበኛ ኢንቨስተሮች"** ማለት በሕዝብ ሽያጭ መመሪያው አንቀጽ 2(49) ሥር የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል።

23/ **"ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2(62) ሥር የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል።

24/ **"የቴክኒክ አጋር"** ማለት ከገንዘብ አሰባሳቢው ንግድ ጋር አግባብነት ያለው ሊረጋገጥ የሚችል ሙያዊ ብቃት፣ የዘርፉ ልምድ ወይም ልዩ ዕውቀት ያለው ሰው ሆኖ፡-

ሀ) በሚመለከተው ዘርፍ ወይም መስክ ቢያንስ የሁለት (2) ዓመት የሥራ ልምድ ያለው፤

ለ) ለገንዘብ አሰባሳቢው ጉልህ የቴክኒክ ድጋፍ፣ ስትራቴጂካዊ ግብዓት ወይም የአሠራር መመሪያ የሚሰጥ፤ እና

ሐ) በገንዘብ አሰባሳቢው ውስጥ የባለቤትነት ድርሻ ሊኖረውም ላይኖረውም የሚችል ሆኖ፣ የገንዘብ አሰባሳቢውን የንግድ ሞዴል በማዳበር፣ በመተግበር ወይም በማስፋፋት ውስጥ ወሳኝ ሚና የሚጫወት ነው።

25/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም ህጋዊ ሰውነት ያለው ሰው ነው።

26/ በዚህ መመሪያ፣ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተቀመጠ አገላለጽ ሁሉ የሴትንም ጾታ ይጨምራል።

27/ በዚህ መመሪያ ላይ የዋለ ማንኛውም ቃል በአዋጁ ላይ የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል።

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚካሄድ ኢንቨስትመንት ክራውድ ፈንዲንግ እና በእዛም ላይ በሚሳተፉ ሁሉም ሰዎች ማለትም በባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጣቸው የክራውድ ፈንዲንግ አገናኞች፣ በእነዚህ አገናኞች በሚንቀሳቀሱ የክራውድ ፈንዲንግ መድረኮች አማካኝነት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለሽያጭ የሚያቀርቡ ገንዘብ አሰባሳቢዎችን እና ሽያጭ አቅርቦቶች ላይ የሚሳተፉ ኢንቨስተሮላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

# ምዕራፍ ሁለት ፤ ገንዘብ አሰባሳቢዎችና ኢንቨስተሮች

## ክፍል 1፤ ገንዘብ አሰባሳቢዎች

### 4. ብቁ ገንዘብ አሰባሳቢዎች

ድርጅቱ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ በክራውድፈንዲንግ መድረክ በኩል ገንዘብ ለመሰብሰብ ብቁ ይሆናል፡-

1. በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሠረት የተቋቋመና የተመዘገበ አክሲዮን ማህበር ከሆነ፤ እና
2. በማመልከቻው ወቅት ከሚከተሉት ሦስት (3) የፋይናንስና የአሰራር መስፈርቶች ቢያንስ ሁለቱን (2) የሚያሟላ ከሆነ፡-

   ሀ. ጠቅላላ የተከፈለ ካፒታሉ ከሃምሳ ሚሊዮን ብር (50,000,000 ETB) የማይበልጥ፤

   ለ. ጠቅላላ የተጣራ ሀብቱ (የአክሲዮን ካፒታል፣ ያልተከፋፈለ የተያዘ ትርፍ እና የተያዙ ተጠባባቂዎችን ጨምሮ) ከአንድ መቶ ሚሊዮን ብር (100,000,000 ETB) የማይበልጥ፤ ወይም

   ሐ. ዓመታዊ የተጣራ ሽያጩ ከአንድ መቶ ሚሊዮን ብር (100,000,000 ETB) የማይበልጥ።

### 5. ብቁ ያልሆኑ ገንዘብ አሰባሳቢዎች

1/ የሚከተሉት ድርጅቶች በክራውድ ፈንዲንግ መድረክ አማካኝነት ገንዘብ ለማሰባሰብ ብቁ አይደሉም፡-

ሀ) የፋይናንስ ተቋማት፤

ለ) የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች፤

ሐ) የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና ተቀጽላዎቻቸው፤

መ) የህዝብ ኩባንያዎችና ተቀጽላዎቻቸው፤

ሠ) የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንዶች፤

ረ) ከኢትዮጵያ ውጭ የተቋቋሙ ድርጅቶች፤ እና

ሸ) ከጊዜ ወደ ጊዜ በባለሥልጣኑ የሚወሰን ሌላ ማንኛውም ሰው።

2/ ድርጅቱ ዳይሬክተሮቹ፣ መሥራቾቹ ወይም ድርጅቱን ለመቆጣጠር የሚያስችል የአክሲዮን ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖቹ በማታለል፣ በፋይናንስ ብልሹ አሠራር፣ በሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር፣ በሽብርተኝነት የገንዘብ ድጋፍ ወይም በካፒታል ገበያ ወንጀሎች ጥፋተኛ የተባሉበት ወይም ባለፉት [5]

ዓመታት ውስጥ ማንኛውንም የካፒታል ገበያ ሕጎችና ደንቦች የጣሰ ገንዘብ አሰባሳቢ በክራውድ ፈንዲንግ አማካኝነት ገንዘብ ለማሰባሰብ ብቁ አይደለም።

3/ የክራውድ ፈንዲንግ ሽያጭ አቅርቦት እያካሄደ ያለ ሰው ቀደም ያለው አቅርቦት እስኪጠናቀቅ፣ እስኪነሳ፣ እስኪሰረዝ ወይም በሌላ ሁኔታ እስኪዘጋ ድረስ ሌላ የክራውድ ፈንዲንግ ሽያጭ አቅርቦት ማስጀመር አይችልም።

## 6. በክራውድ ፈንዲንግ መድረክ የመመዝገብ ግዴታ

1/ በክራውድ ፈንዲንግ መድረክ አማካኝነት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለማቅረብ የሚጠይቅ ማንኛውም ገንዘብ አሰባሳቢ ማንኛውም ዓይነት አቅርቦት ከመፈጸሙ በፊት በክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ መመዝገብ አለበት።

2/ ምዝገባው በመድረኩ በኦንላይን ሥርዓት ወይም በባለሥልጣኑ በተፈቀዱ ሌሎች ዘዴዎች መከናወን አለበት።

## 7. የምዝገባ መስፈርቶች

ገንዘብ አሰባሳቢዎች ቢያንስ የሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱንና በዚህ መመሪያ ምዕራፍ አምስት ሥር የተመለከቱትን ተያያዥ ሰነዶች በክራውድ ፈንዲንግ መድረኩ አማካኝነት ለክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ማቅረብ አለባቸው።

## 8. ገንዘብ የማሰባሰብ ጣሪያ

1/ በአንድ ገንዘብ አሰባሳቢ በአሥራ ሁለት ወራት ውስጥ ሊሰበሰብ የሚችለው ጠቅላላ የገንዘብ መጠን በአንድ ዓመት ውስጥም ሆነ በድምር ከሚከተለው መብለጥ የለበትም፦

ሀ) ለምድብ አንድ ገንዘብ አሰባሳቢ 10 [አሥር] ሚሊዮን ብር፤

ለ) ለምድብ ሁለት ገንዘብ አሰባሳቢ 25 [ሃያ አምስት] ሚሊዮን ብር፤ እና

ሐ) ለምድብ ሦስት ገንዘብ አሰባሳቢ 50 [ሃምሳ] ሚሊዮን ብር።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም፣ አንድ ገንዘብ አሰባሳቢ በክራውድ ፈንዲንግ መድረክ አማካኝነት የሚሰበስበው ጠቅላላ የገንዘብ መጠን ከሃምሳ [50] ሚሊዮን ብር መብለጥ የለበትም።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከቱት የገንዘብ ማሰባሰቢያ ጣሪያዎች ስሌት ገንዘብ አሰ ባሳቢው በሁሉም የክራውድ ፈንዲንግ መድረኮች ያቀረባቸውን አቅርቦቶች ድምር ውጤት ላይ የተመሰረተ ።

4/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን የገንዘብ ጣሪያዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ በጋይድላይን ሊያሻሽል ይችላል።

## ክፍል 2፤ ኢንቨስተሮች

### 9. ብቁ ኢንቨስተሮች

በክራውድ ፈንዲንግ መድረክ አማካኝነት በሚቀርቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ኢንቨስት ለማድረግ የሚችሉ የኢንቨስተር ምድቦች የሚከተሉት ናቸው፡-

1) መደበኛ ኢንቨስተሮች፤ እና

2) ብቁ ኢንቨስተሮች።

### 10. የኢንቨስትመንት ገደቦች

1/ በመደበኛ ኢንቨስተሮች ላይ የሚከተሉት የኢንቨስትመንት ገደቦች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡-

ሀ) በአንድ የሽያጭ አቅርቦት ከፍተኛው የኢንቨስትመንት መጠን የኢንቨስተሩን አመታዊ የተጣራ ገቢ 5 በመቶ ፤

ለ) በሁሉም የክራውድ ፈንዲንግ መድረኮች በዓመት በድምር የኢንቨስተሩን አመታዊ የተጣራ ገቢ 10 በመቶ።

2/ መደበኛ ኢንቨስተሮች በክራውድ ፈንዲንግ አማካኝነት በሚቀርብ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ላይ ኢንቨስት ከማድረጋቸው በፊት በክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ የሚቀርበውን የስጋት መረዳትን ማረጋገጫና የተስማሚነት ግምገማ ማጠናቀቅ አለባቸው።

3/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን የኢንቨስትመንት ጣሪያዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ በጋይድላይን ሊያሻሽል ይችላል።

### 11. የኢንቨስተር ምዝገባ

ሁሉም ኢንቨስተሮች ማንኛውንም ኢንቨስትመንት ከማድረጋቸው በፊት፣ ማመልከቻ በማቅረብና በክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ግምገማና ይሁንታ መሠረት፣ በክራውድ ፈንዲንግ መድረኩ የኦንላይን ሥርዓት ወይም በባለሥልጣኑ በተፈቀደ ማንኛውም ሌላ ዘዴ መሰረት መመዝገብ አለባቸው።

## ምዕራፍ ሦስት ፤ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ ግዴታዎች

### 12. አጠቃላይ ግዴታ

1/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ የኢንቨስተሮችን ጥቅም ለማስጠበቅ ምክንያታዊና አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን በሙሉ መውሰድ አለበት።

2/ በፈቃድ አሰጣጥ መመሪያው አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ፡-

ሀ) መድረኩን የሚጠቀሙ ኢንቨስተሮችንና ገንዘብ አሰባሳቢዎችን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ በታማኝነትና ፍትሐዊነት መሥራት አለበት፤

ለ) በመድረኩ አማካኝነት የሚፈጸሙ የማታለል፣ የሸፍጥ ወይም አሳሳች ተግባራትን ለመለየት፣ ለመከላከል እና ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችሉ ተገቢ ዘዴዎችን መዘርጋት አለበት፤

ሐ) ከመድረኩና ከአጠቃቀሙ ጋር የተያያዙ አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በመድረኩ ላይ ይፋ ማድረግና ማሳየት አለበት፤ እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

i. መድረኩ እንዴት እንደሚሠራ፤

ii. የተጠቃሚዎች መብትና ግዴታዎች፤

iii. በመድረኩ ገንዘብ ማሰባሰብ የሚፈልጉ ገንዘብ አሰባሳቢዎችና ኢንቨስተሮች የብቁነት መስፈርቶች ዝርዝር፤

iv. የኢንቨስተሮች ማስተማሪያ፤

v. በመድረኩ አማካኝነት በክራውድ ፈንዲንግ ስለመሳተፍ የሚሰጥ አጠቃላይ የስጋት ማስጠንቀቂያ፤

vi. የገንዘብ አሰባሳቢውን ንግድ ሕጋዊነት ማረጋገጡን የሚገልጽ ማረጋገጫ፤

vii. በመድረኩ አማካኝነት ለሚቀርቡ ቅሬታዎች አቀራረብ፤ አያያዝና አለመግባባቶችን የመፍቻ አሰራሮች፤ እና

viii. መድረኩን በመጠቀማቸው ምክንያት በገንዘብ አሰባሳቢው ወይም በኢንቨስተሩ ላይ ሊጣሉ የሚችሉ ተያያዥ ክፍያዎች፣ አገልግሎት ክፍያዎችና ወጪዎች።

መ) ገንዘብ አሰባሳቢውና ኢንቨስተሮች በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን ገደቦች፣ ኃላፊነቶችና ግዴታዎች ሙሉ በሙሉ ማክበራቸውን ማረጋገጥ አለበት፤

ሠ) የገንዘብ አሰባሳቢው የመረጃ ይፋ ማድረጊያ ሰነድ ትክክለኛነቱ መረጋገጡንና በመድረኩ አማካኝነት ለኢንቨስተሮች ተደራሽ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፤

ረ) በዚህ መመሪያ ሥር እንደተመለከተው በገንዘብ አሰባሳቢው የሽያጭ ማቅረቢያ ሰነድ ላይ የሚደረግ ማንኛውንም ወሳኝ ለውጥ ለኢንቨስተሮች ማሳወቅ አለበት፤

ሰ) በባለሥልጣኑ ሊጠየቅ የሚችለውን ማንኛውንም ሌላ ግዴታ መወጣት አለበት።

3/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ የተፈቀዱለትን ተግባራት በአስተማማኝ፣ በቀልጣፋና በአግባቡ ለማከናወን የሚያስችል ብቃት፣ ሙያዊ ዕውቀትና ልምድ ያላቸውን በቂ ቁጥር ያላቸው ሠራተኞች በማንኛውም ጊዜ መያዝ አለበት።

4/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ዓላማ፣ በፈቃድ አሰጣጥ መመሪያው ሥር የተጣሉት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ የሥራውን ባህርይ፣ መጠንና ውስብስብነት ከግምት በማስገባት የሚከተሉትን ተሿሚ እንደራሴዎች መሾም ወይም መመደብ አለበት፡-

ሀ) ከሥራው የሚመነጩ ስጋቶችን የመለየት፣ የመገምገምና የማስተዳደር ኃላፊነት ያለው ዋና የስጋት ኃላፊ፤

ለ) የክራውድ ፈንዲንግ መድረኩን ጥገና፣ አሠራርና ደኅንነት በተመለከተ ኃላፊነት ያለው ዋና የቴክኖሎጂ ኃላፊ፤

ሐ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 ሥር የተመለከተውን የተገቢነት ቁመና ጥናት የማካሄድ ኃላፊነት ያለው ዋና የተገቢነት ቁመና ጥናት ኃላፊ፤ እና 5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት የተሾመ ወይም የተመደበ ሰው በፈቃድ አሰጣጥ መመሪያው ሥር በተሿሚ እንደራሴዎች ላይ ተፈጻሚ የሆኑትን የብቁ እና ተገቢነት መስፈርቶችን ማሟላት አለበት።

## 13. የተገቢነት ቁመና ጥናት

1/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ መድረኩን ለመጠቀም በሚፈልጉ ገንዘብ አሰባሳቢዎች ላይ የተገቢነት ቁመና ጥናት ማካሄድ አለበት።

2/ ዝቅተኛ የተገቢነት ቁመና ጥናት መስፈርቶች የሚከተሉትን ለማድረግ ምክንያታዊ እርምጃዎችን መውሰድን ያካትታሉ፡-

ሀ) የገንዘብ አሰባሳቢውን ሕጋዊ ምስረታና የስራ ፈቃዶች ማረጋገጥ፤

ለ) ገንዘብ የማሰባሰብ ብቁነቱን ማረጋገጥ፤

ሐ) የታቀደው የገንዘብ ማሰባሰብ ሕጋዊነትን ማረጋገጥ፤

መ) ከማጭበርበር፣ ከእምነት ማጉደል፣ ከካፒታል ገበያ ጥሰቶች፣ ከሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር ወይም ከሽብርተኝነት የገንዘብ ድጋፍ ጋር በተያያዘ የተላለፉ ቅጣቶችን፣ የቁጥጥር ማዕቀቦችን ወይም በመታየት ላይ ያሉ ምርመራዎችን ጨምሮ የገንዘብ አሰባሳቢውን ዳይሬክተሮችና ተቆጣጣሪ ባለአክሲዮኖች ብቁ እና ተገቢ ሰው መሆናቸውን መገምገም፤

ሠ) የገንዘብ አሰባሳቢውን የሚከተሉት ትክክለኛነት ማረጋገጥ፡-

i) የንግድ ሐሳብ፤

ii) የፋይናንስ ሁኔታ፤ እና

iii) የመክፈል አቅም፤

ረ) አግባብነት ባለው ሁኔታ፣ ሕጋዊ ህልውናቸውን፣ የሥራ ልምዳቸውን፣ የፋይናንስ አቅማቸውንና ብቁ እና ተገቢ ሰው መሆናቸውን ማረጋገጥን ጨምሮ በገንዘብ አሰባሳቢው የቴክኒክ አጋሮችና ቁልፍ ኢንቨስተሮች ላይ የተገቢነት ቁመና ጥናት ማካሄድ፤

ሰ) ገንዘብ አሰባሳቢው ወይም አቅርቦቱ እንደ የዘላቂነት ወይም የሸሪዓ መርሆዎችን የሚከተሉ ተግባራትን ጨምሮ ልዩ ተግባራትን የሚመለከት ከሆነ፣ እነዚያ ተግባራት ወይም አቅርቦቶች እነዚህ ተግባራት ወይም አቅርቦቶችን በተመለከተ ከወጡ ህጎች እና መርሆዎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ እና

ሸ) በዚህ መመሪያ ሥር የተመለከቱትን የመረጃ ይፋ ማድረግ መስፈርቶች ማክበሩን መገምገም።

## 14. ገንዘብ አሰባሳቢዎችን መመዝገብ

1/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ሥር የተመለከተውን የገንዘብ አሰባሳቢዎች ማመልከቻ በማስተናገድ ማመልከቻውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በአርባ አምስት (45) ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት።

2/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ የምዝገባ ማመልከቻውን ሊያጸድቅ ወይም ውድቅ ሊያደርግ ይችላል።

3/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ የገንዘብ አሰባሳቢውን ማመልከቻ ውድቅ ሊያደርግ የሚችለው፡-

ሀ) ገንዘብ አሰባሳቢው በዚህ መመሪያ ሥር የተመለከቱትን የብቁነት መስፈርቶች ማሟላት ካልቻለ፤

ለ) የቀረበው መረጃ ወይም ሰነድ ያልተሟላ፣ ትክክለኛ ያልሆነ፣ ሐሰተኛ ወይም አሳሳች ከሆነ፤

ሐ) ገንዘብ አሰባሳቢው ሕገወጥ በሆኑ ወይም አግባብነት ካላቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ወይም የካፒታል ገበያ ሕጎች ጋር በሚቃረኑ ተግባራት ላይ የተሰማራ ከሆነ ወይም እንደተሰማራ በምክንያታዊነት ከተጠረጠረ፤

መ) ገንዘብ አሰባሳቢው፣ ዳይሬክተሮቹ ወይም ተቆጣጣሪ ባለአክሲዮኖቹ በዚህ መመሪያ የሚጠየቀውን የብቁ እና ተገቢነት መስፈርቶችን ካላሟሉ፤

ሠ) ገንዘብ አሰባሳቢው በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን የተገቢነት ቁመና ጥናት መስፈርቶች ካላሟላ፤ ወይም

ረ) ገንዘብ አሰባሳቢው በባለሥልጣኑ ወይም በክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ የተደነገጉትን ማንኛውንም ተጨማሪ መስፈርቶች ካላሟላ ነው።

4/ ማመልከቻው ውድቅ በሚደረግበት ጊዜ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ ውድቅ የተደረገበትን ምክንያት ጨምሮ ለገንዘብ አሰባሳቢው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።

## 15. በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ይሁንታ

1/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ ማንኛውንም ገንዘብ አሰባሳቢ ከመመዝገቡ በፊት፣ የገንዘብ አሰባሳቢውን ምዝገባ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ እና የገንዘብ አሰባሳቢውን ብቁነት የሚያረጋግጡ ደጋፊ ሰነዶችን፣ የሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱን እና የሚጠበቅበትን የተገቢነት ቁመና ጥናት ማካሄዱን የሚገልጽ ማረጋገጫ ጨምሮ ማቅረብ አለበት።

2/ ባለሥልጣኑ በማመልከቻው ላይ ሊኖረው የሚችለውን ማንኛውንም ተቃውሞ በሃያ (20) ቀናት ውስጥ ማሳወቅ አለበት። በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ ካልተገለጸ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ገንዘብ አሰባሳቢውን ይመዘግባል።

## 16. ኢንቨስተሮችን የመመዝገብ ግዴታዎች

1/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ በኢንቨስተሮች የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን በዚህ መመሪያ መሠረት በማስተናገድ በአግባቡ የተሞላ ማመልከቻ ከደረሰው በኋላ በምክንያታዊ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት።

2/ በፈቃድ አሰጣጥ መመሪያውና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች ሥር ከተመለከቱት የደንበኛህን ዕወቅ፣ የሕገወጥ የገንዘብ ዝውውርን የመከላከልና የሽብርተኝነት የገንዘብ ድጋፍን የመከላከል መስፈርቶች በተጨማሪ፣ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ኢንቨስተሮች ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች እንዲያቀርቡ መጠየቅ አለበት፡-

ሀ) ሙሉ ስምና የፋይዳ (ብሔራዊ) መታወቂያ ቁጥር፤

ለ) የገንዘብ ምንጭ መግለጫ፤

ሐ) በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ያለው የቀድሞ የኢንቨስትመንት ልምድ፤ እና

መ) በክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ወይም በባለሥልጣኑ የሚጠየቅ ማንኛውም ተጨማሪ ሰነድ።

3/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ የኢንቨስተሮችን የምዝገባ ማመልከቻ ሊያጸድቅ ወይም ውድቅ ሊያደርግ ይችላል።

4/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ የኢንቨስተሩን ማመልከቻ ውድቅ ሊያደርግ የሚችለው፡-

ሀ) ኢንቨስተሩ በዚህ መመሪያ ሥር የተመለከቱትን የብቁነት መስፈርቶች ማሟላት ካልቻለ፤

ለ) የቀረበው መረጃ ወይም ሰነድ ያልተሟላ፣ ትክክለኛ ያልሆነ፣ ሐሰተኛ ወይም አሳሳች ከሆነ፤

ሐ) ኢንቨስተሩ በፈቃድ አሰጣጥ መመሪያው ወይም በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተደነገጉትን ደንበኛህን ዕወቅ፣ የገንዘብ ሕገወጥ ዝውውርን የመከላከልና የሽብርተኝነት የገንዘብ ድጋፍን የመከላከል መስፈርቶች ካላሟላ፤ ወይም

መ) ኢንቨስተሩ በባለሥልጣኑ ወይም በክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ የተደነገጉትን ማንኛውንም ተጨማሪ መስፈርቶች ካላሟላ ነው።

5/ ማመልከቻው ውድቅ በሚደረግበት ጊዜ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ውድቅ ማድረጉን እና ውድቅ ያደረገበትን ምክንያት ለኢንቨስተሩ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።

## 17. ስጋትን ይፋ የማድረግ ግዴታዎች

1/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ ኢንቨስተሮች በክራውድ ፈንዲንግ መድረኩ ላይ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ከመፍቀዱ በፊት፦ሀ) ኢንቨስተሮች በመድረኩ ላይ ስለሚቀርቡ ኢንቨስትመንቶች ባህርይ እና ስጋቶች ትምህርት ወይም መመሪያ ማግኘታቸውን፤

ለ) ኢንቨስተሮች የመድረኩን የስጋት መግለጫ ማግኘታቸውን እና መረዳታቸውን በግልጽ ማረጋገጣቸውን፤

ሐ) ኢንቨስተሮች በመድረኩ አማካኝነት ከሚያደርጉት ኢንቨስትመንት ሊደርስባቸው የሚችለውን ኪሳራ ለመቋቋም በቂ የፋይናንስ አቅም እንዳላቸው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 18 መሠረት ማወጃቸውን፤

ማረጋገጥ አለበት።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ለ) መሰረት የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ የሚሰጠው የስጋት መግለጫ ከክራውድ ፈንዲንግ ኢንቨስትመንቱ ጋር የተያያዙ ስጋቶችን የሚከተሉትን መረጃዎች ያካትታል፡-

ሀ) በመድረኩ አማካኝነት ኢንቨስት ስለማድረግ የሚሰጥ የማስጠንቀቂያ መግለጫ፤

ለ) ኢንቨስትመንቱን የማውጣት አቅም ላይ ያሉ ገደቦች፤ እና

ሐ) ማንኛውም ሌላ ተገቢ የስጋት መግለጫ።

3/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ የማስጠንቀቂያ መግለጫው በሚከተሉት ቦታዎች በጉልህ መቀመጡን ማረጋገጥ አለበት፡-

ሀ) በመድረኩ የመነሻ ገጽ ላይ ለሁሉም ጎብኝዎች፤

ለ) ለእያንዳንዱ ኢንቨስተር፣ በእያንዳንዱ ገንዘብ አሰባሳቢ የግዢ ቃል ኪዳን መስጫ ገጽ ላይ፤ እና

ሐ) በመድረኩ አማካኝነት ኢንቨስት ለማድረግ በሚያገለግሉ ሁሉም የማመልከቻ ቅጾች ላይ።

4/ የሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዶችን፣ የስጋት ማስጠንቀቂያዎችንና የማስጠንቀቂያ መግለጫዎችን ጨምሮ ሁሉም ቁልፍ የመረጃ ይፋ ማድረጊያዎች ቢያንስ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች መቅረብ አለባቸው።

## 18. የስጋት ማረጋገጫ ቅጽ

1/ መደበኛ ኢንቨስተሮች በክራውድ ፈንዲንግ አማካኝነት በሚቀርብ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ላይ ኢንቨስት ከማድረጋቸው በፊት በክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ የሚቀርበውን ስጋቱን መረዳታቸውን ማረጋገጫ እና ኢንቨስትመንቱን የተስማሚነት ግምገማ ቅጽ መሙላት እና መፈረም አለባቸው።

2/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰውን የተጠቀሰው ቅጽ የሚከተሉትን መረጃዎች

ሀ) የታቀደውን ኢንቨስትመንትና ከእርሱ ጋር የተያያዙ ስጋቶችን መረዳቱን፤

ለ) የክራውድ ፈንዲንግ ኢንቨስትመንቶች በአዋጁ መሠረት በተቋቋመው የኢንቨስተሮች ካሳ ፈንድ የማይሸፈኑ መሆናቸውን መረዳቱን፤

ሐ) ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ ላይ የዝውውር ገደቦች ሊጣሉ የሚችሉ መሆኑን መረዳቱን፤

መ) ኢንቨስት ያደረገውን ገንዘብ በሙሉ ቢያጣ የመሸከም የፋይናንስ አቅም ያለው መሆኑን፤

ሠ) ኢንቨስት ሊያደርገው ያሰበው መጠን በአንቀጽ 10 ላይ የሰፈረወን ድንጋጌ የማይጥስጥ መሆኑን፤ እና

ረ) ከሽያጭ አቅርቦቱ ጋር በተያያዘ የሚጠየቁት የመረጃ ይፋ ማድረጊያዎች በሙሉ የቀረቡለት መሆኑን፤

መያዝ አለበት።

2/ በስጋት ማረጋገጫ ቅጹ ውስጥ የተካተተው መረጃ ኢንቨስተሩ በቀላሉ ሊያነበው እና ሊረዳው በሚያስችል መልኩ መዘጋጀት አለበት።

3/ የስጋት ማረጋገጫ ቅጽ ለኢንቨስተሩ ቢያንስ በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ መቅረብ አለበት፤ ኢንቨስተሩም በመረጠው ቋንቋ የተዘጋጀውን ቅጅ ይፈርማል።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የሚጠየቀው ማረጋገጫ በኤሌክትሮኒክ መንገድ ወይም በባለሥልጣኑ በተፈቀደ በማንኛውም ሌላ መልኩ፣ ሰነዱ ሙሉ በሙሉ ተደራሽ መሆኑንና አገልግሎቱን ከመጠቀም ጋር ከተያያዘ ማንኛውም ስምምነት ተለይቶ መፈረሙን በሚያረጋግጥ ሂደት መገኘት አለበት።

## 19. የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ በአቅርቦት ጊዜ ውስጥ ያሉበት ግዴታዎች

1/ በሽያጭ አቅርቦት ወቅት የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ፡-

ሀ) እጩ ኢንቨስተሮች በማንኛውም ጊዜ የሚከተሉትን ማድረግ መቻላቸውን ማረጋገጥ:-

i. የክራውድ ፈንዲንግ መድረኩን መጠቀም፤

ii. ከሽያጭ አቅርቦቱ ጋር የተያያዙ ማመልከቻዎችን ማቅረብ፤

iii. ከሽያጭ አቅርቦቱ ጋር የተያያዙ ማመልከቻዎቻቸውን ማየት እና መከታተል፤ እና

iv. ከሽያጭ አቅርቦቱ ጋር የተያያዙ ማንኛውም ጥያቄዎችን መጠየቅ።

ለ) አንድ መደበኛ ኢንቨስተር የስጋት ማረጋገጫ ቅጽ ካልሞላ በስተቀር በክራውድ ፈንዲንግ መድረኩ አማካኝነት ከማንኛውም የክራውድ ፈንዲንግ ሽያጭ አቅርቦት ጋር በተያያዘ የኢንቨስትመንት ማመልከቻ አለማቅረቡን ማረጋገጥ፤ እና

ሐ) ከክራውድ ፈንዲንግ መድረኩ ውጪ በሌላ መንገድ የቀረበ ማንኛውንም ማመልከቻ ውድቅ ማድረግ፣

አለበት።

2/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ በማንኛውም ጊዜ የሚከተሉት በእያንዳንዱ የሽያጭ አቅርቦት በሚገኝበት መድረክ የመጀመሪያ ገጽ ላይ በጉልህ መታየታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡-

ሀ) በክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ የሚጣሉ ክፍያዎች፤ እና

ለ) የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ወይም ተባባሪዎቹ በሽያጩ ላይ ያላቸውን ወይም ሊያገኙ የሚጠብቁትን ማንኛውንም ቀጥተኛ ወይም ተዘዋዋሪ የገንዘብ ጥቅም ይፋ ማድረግ።

ሐ) መደበኛ የማስጠንቀቂያ መግለጫዎች፣ እና ከእነዚሁ ጋር ተያይዘው ወደሚከተሉት በቀጥታ የሚያስገናኙ የድር አገናኞች፦

**i.** የአቅርቦት ሰነዱ እና ተያያዥ የሆኑ መረጃዎች የሚገኙበት ገጽ፤

**ii.** የስጋት ማረጋገጫ ቅጽ ፤

**iii.** የኢንቨስተር ትምህርት መድረክ፤ እና

**iv.** በዚህ መመሪያ መሠረት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተያያዥ መረጃዎች።

## 20. የመረጃ ጥበቃና ግለዊነት

የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ፡-

1/ የሚቀበለውና ይፋ የሚያደርገው መረጃ ተዓማኒነቱ የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ተገቢ የጥበቃ ዘዴዎችን መዘርጋት አለበት።

2/ ከኢንቨስተሮች የተሰበሰበው መረጃ ደኅንነትና ምስጢራዊነት መጠበቁን ማረጋገጥ አለበት።

3/ ተስማሚ የመጠባበቂያ አገልግሎቶችን መዘርጋትና ሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ አለበት።

4/ የአሠራር ስጋቶችን ምንጮች መለየትና የአሠራር መስተጓጎልን ለማስወገድ በቂ ሥነ-ሥርዓቶችንና ቁጥጥሮችን መዘርጋት አለበት።

5/ እያንዳንዱ ኢንቨስተር በመድረኩ የተያዘውን የግል መዝገቡንና የኢንቨስትመንት ታሪኩን በቀጣይነትና በአስተማማኝ ሁኔታ ማግኘት መቻሉን ማረጋገጥ አለበት።

6/ አግባብነት ያላቸውን የመረጃ ጥበቃና ተያያዥ ሕጎች በሙሉ ማክበር አለበት።

## 21. የጥቅም ግጭት አፈታት

1/ ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያው አንቀጽ 71 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ለራሱ ወይም ከእርሱ ጋር ተዛማጅ ለሆኑ ወገኖች በራሱ መድረክ በኩል ገንዘብ ማሰባሰብ ወይም እንዲያሰባስቡ ማመቻቸት የለበትም።

2/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ በመድረኩ ላይ በቀረበ ማንኛውም የሽያጭ አቅርቦት ላይ ለኢንቨስተር ምንም ዓይነት የኢንቨስትመንት የውሳኔ ሃሳብ ወይም ምክር መስጠት የለበትም።

3/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 29 መሠረት ይፋ ከተደረጉት የመደበኛ መድረክ አገልግሎት ክፍያዎች ውጪ፣ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ከሚሰበሰበው የገንዘብ መጠን ላይ ተመስርቶ የሚከፈል ማንኛውንም ዓይነት ክፍያ፣ ከአቅርቦቱ ስኬት ጋር የተገናኘ ክፍያ ወይም አበል መቀበል የለበትም።

4/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ሊከሰቱ የሚችሉ የጥቅም ግጭቶችን ለመለየት፣ ለመከላከል እና ለማስተዳደር የሚያስችል በጽሁፍ የተዘጋጀ የጥቅም ግጭት ፖሊሲ ማውጣት፣ መተግበር እና ማስፈጸም ያለበት ሲሆን፣ የተለዩ የጥቅም ግጭቶችን ለማስወገድ የተወሰዱ እርምጃዎችን ዝርዝር መዝገብ አዘጋጅቶ መያዝ አለበት።

## 22. የተፈቀደ ድጋፍ አገልግሎት

1/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ  ገንዘብ አሰባሳቢን ፤ የሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱንና ተያያዥ ሰነዶችን በማዘጋጀት ጨምሮ፣ የሽያጭ አቅርቦት ላይ በሚደረግ ዝግጅት ሊያግዝ ይችላል፤ ሆኖም፡-

ሀ) የሰጠውን ድጋፍና ለዚሁ የተቀበለውን ማንኛውንም ክፍያ ወይም ጥቅም በሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱ ውስጥና በክራውድ ፈንዲንግ መድረኩ የሽያጭ አቅርቦቱ በሚገኝበት ገጽ ላይ ይፋ ማድረግ፤

ለ) ራሱ ላዘጋጃቸው ወይም ላረጋገጣቸው መረጃዎች ትክክለኛነትና ሙሉነት ከገንዘብ አሰባሳቢው ጋር በጋራ ኃላፊነት መውሰድና ይህንኑ ኃላፊነት በሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱ ውስጥ መግለጽ፤

አለበት።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1  መሠረት የሚሰጥ ድጋፍ በአዋጁ ወይም በፈቃድ አሰጣጥ መመሪያው ሥር የተለየ ፈቃድ ወደሚያስፈልገው ማንኛውም ተግባር ሊዘልቅ አይችልም።

## 23. የቅሬታ አያያዝ

የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ፡-

1/ ከኢንቨስተሮች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በፍጥነት፣ በፍትሐዊነትና በወጥነት ለማስተናገድ ውጤታማና ግልጽ የሆኑ አሰራሮችን መዘርጋትና የእነዚህን ሥነ-ሥርዓቶች መግለጫ ይፋ ማድረግ አለበት።

2/ ኢንቨስተሮች በገንዘብ አሰባሳቢዎች ወይም በክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ላይ ያለ ክፍያ ቅሬታ ማቅረብ መቻላቸውን ማረጋገጥ አለበት።

3/ ሁሉንም ቅሬታዎች በወቅቱና በፍትሐዊነት መርምሮ ውጤቱን በምክንያታዊ ጊዜ ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት።

4/ ኢንቨስተሮች በሽያጭ አቅርቦቶችና በገንዘብ አሰባሳቢዎች ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ዕድል የሚሰጥ፣ ለኢንቨስተሮችና ለገንዘብ አሰባሳቢዎች የሚያገለግል ቁጥጥር የሚደረግበት መስተጋብራዊ መድረክ በክራውድ ፈንዲንግ መድረኩ ላይ ማመቻቸት አለበት፤ ይህም በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፦

ሀ) ገንዘብ አሰባሳቢው ከሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱ፣ ከክራውድ ፈንዲንግ መድረኩ የሥነ-ምግባር ደንቦች ወይም ከዚህ መመሪያ ጋር የማይጣጣም መግለጫ የማይሰጥ ወይም መረጃ የማያቀርብ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚቀርቡ ጽሑፎች ክትትል የሚደረግባቸው መሆኑ፤

ለ) ሐሰተኛ፣ አታላይ ወይም አሳሳች መግለጫ ወይም መረጃ የያዘ ወይም የወሳኝ መረጃ ሐሰተኛ ወይም የተሳሳተ አቀራረብ ወይም መግለጫ ሊሆን የሚችል ማንኛውም ይዘት የተከለከለ መሆኑ፤

ሐ) ገንዘብ አሰባሳቢዎች ለጥያቄዎች በክራውድ ፈንዲንግ መድረኩ ላይ ምላሽ የሚሰጡ መሆኑ መረጋገጡ፤

5/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ለመስተጋብራዊ መድረኩ የሚመራበትን ሥነ_ስርዓት ከማውጣትና ይፋ ከማድረግ እንዲሁም አጸያፊ ወይም አጭበርባሪ ሊሆኑ የሚችሉ መልዕክቶችን ከማስወገድ በስተቀር በመድረኩ ላይ በሚደረጉ ግንኙነቶች መሳተፍ የለበትም።

## 24. የመዝገብ አያያዝ ግዴታዎች

1/ በፈቃድ አሰጣጥ መመሪያው አንቀጽ 73 ሥር የተመለከቱት የመዝገብ አያያዝ ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ የሚከተሉትን ተጨማሪ መዛግብት መያዝና መጠበቅ አለበት፦

ሀ) በመድረኩ ላይ ከሚደረጉ የኢንቨስተሮችና የገንዘብ አሰባሳቢዎች እንቅስቃሴዎች ጋር የተያያዙ መረጃዎች እና መዝገቦችን፤

ለ) በመድረኩ ላይ የተከሰቱ ሁሉንም ብልሽቶች፣ የተከናወኑ ጥገናዎችንና የውስጥ ለውጥ መረጃዎችን፤

ሐ) በመስተጋብራዊ መድረኩ ላይ ወይም በመድረኩ አማካኝነት የተደረጉ ሁሉንም ግንኙነቶች የሚመለከቱ መረጃዎችን፤

መ) የደረሱትን ቅሬታዎች በሙሉና የተወሰዱትን እርምጃዎች፤

ሠ) የግዢ ቃል ኪዳኖችንና ለእያንዳንዱ ኢንቨስተር የተደለደሉትን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ብዛት፣ የሁሉንም የድልድል እርምጃዎች፣ የኦዲት መዝገብ እንዲሁም የገንዘብ እንቅስቃሴዎችን።

2/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ በክራውድ ፈንዲንግ መድረኩ አማካኝነት የወጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ባለቤቶች መዝገብ የመያዝ ኃላፊነት አለበት፤ መዝገቡም የእያንዳንዱን ሰነደ ሙዓለንዋይ ባለቤት ማንነት፣ የያዘውን ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ብዛት እና ክፍል እንዲሁም የተፈጸመውን እያንዳንዱን ዝውውር የሚያካትት ሆኖ፣ መዝገቡንና በእርሱ ላይ የሚደረግ ማንኛውንም ለውጥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 24 መሠረት ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት።

3/ በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተጣሉ የመዝገብ አያያዝ ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በዚህ መመሪያ መያዝ የሚጠበቅባቸው መዛግብት ቢያንስ ለአሥር ዓመታት መጠበቅ አለባቸው።

## 25. ቀጣይነት ያለው ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ

1/ የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያው አንቀጽ 75 ንዑስ አንቀጽ (2) አጠቃላይ ድንጋጌዎች ሳይወሰን፣ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ በየሩብ ዓመቱ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ማቅረብና መረጃ መስጠት አለበት፡-

ሀ) የተመዘገቡ ገንዘብ ሰብሳቢዎች ዝርዝር እና በመድረኩ አማካኝነት የተሰበሰበው የገንዘብ መጠን፤

ለ) የገንዘብ አሳባሳቢዎችን ምድብ እና የኢንቨስትመንት አዝማሚያዎች ስታቲስቲክስ፤

ሐ) በግብይቶች ብዛት፣ በአንድ ግብይት ውስጥ በተካተቱ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ብዛት እንዲሁም በገንዘብ አሰባሳቢው የተሰበሰበው የተላለፈው ጠቅላላ የገንዘብ መጠን የሚልጽ የግብይት መረጃ፤

መ) የተመዘገቡ ኢንቨስተሮችን፣ ኢንቨስት ያደረጉትን መጠን እና ለኢንቨስተሮች የተደለደሉ እና በኢንቨስተሮች የተያዙ የሰነደ ሙዓለንዋዮች መጠን፤

ሠ) በክራውድ ፈንዲንግ መድረኩ አማካኝነት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የሚያቀርብ ወይም የሚሸጥ እያንዳንዱ ገንዘብ አሰባሳቢ የታለመውን የሽያጭ መጠን ለማሳካት ያለበትን ደረጃ የሚያሳይ መዝገብ፤ እና

ረ) ባለሥልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊጠይቅ የሚችለው ማንኛውም ሌላ መረጃ።

2/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ሥር የተመለከቱትን የገንዘብ ማሰባሰቢያ ጣሪያዎችና በአንቀጽ 10 ሥር የተመለከቱትን የኢንቨስትመንት ጣሪያዎች መከበራቸውን ባለሥልጣኑ በቅጽበት መከታተል እንዲችል፣ ባለሥልጣኑ በአሠራር መመሪያ በሚወስነው ቅርጽና ዘዴ መረጃን በኤሌክትሮኒክ መንገድ የሚያስተላልፍ ሥርዓት መዘርጋትና መጠበቅ አለበት።

## ምዕራፍ አራት ፤ የክራውድ ፈንዲንግ ግብይት

### 26. የተፈቀዱ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች

1/ ገንዘብ አሰባሳቢዎች በክራውድ ፈንዲንግ መድረክ አማካኝነት አክሲዮኖችንና ሌሎች በባለቤትነት ድርሻ ላይ የተመሠረቱ ሰነዶችን ማቅረብ ይችላሉ።

2/ ገንዘብ አሰባሳቢው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 ሥር የተመለከቱትን መስፈርቶች ካሟላ በክራውድ ፈንዲንግ መድረክ አማካኝነት የዕዳ ሰነዶችን ማቅረብ ይችላል።

3/ የዕዳ ሰነዶችን የሚያቀርብ ገንዘብ አሰባሳቢ የሚከተሉትን ማሟላት ይጠበቅበታል፡-

ሀ) በኢትዮጵያ የሒሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ በተቀመጠው ወቅታዊ የሒሳብ አያያዝ ደረጃ መሠረት የተዘጋጀ የሦስት (3) ዓመታት ኦዲት የተደረገ የሒሳብ መግለጫ፤ እና

ለ) የታቀደውን ዕዳ የመክፈል አቅም ያለው መሆን የሚኖርበት ሲሆን፣ ይህም በሚከተሉት ይረጋገጣል፡-

i) ከሽያጭ አቅርቦቱ በፊት ላሉት ሦስት (3) የሒሳብ ዓመታት ትርፋማ መሆን፤

ii) ከሽያጭ አቅርቦቱ በፊት ላሉት ሦስት (3) የሒሳብ ዓመታት አዎንታዊ የገንዘብ ፍሰት መኖር፤ እና

iii) የእዳ ሰነዱን የቆይታ ጊዜ የሚሸፍን የገንዘብ ፍሰት ትንበያ ማቅረብ።

4/ ለዕዳ ሰነዶች ሽያጭ አቅርቦት የሚዘጋጅ የሽያጭ ማቅረቢያ ሰነድ በዚህ መመሪያ ምዕራፍ አምስት ሥር ከተመለከቱት መስፈርቶች በተጨማሪ የሚከተሉትን ይፋ ማድረግ አለበት፡-

ሀ) ዋናውን የገንዘብ መጠን፣ የወለድ ወይም የትርፍ ምጣኔን፣ የቆይታ ጊዜውን፣ የመክፈያ ሰሌዳውን እና የሚቀርብ ማንኛውንም መያዣ ወይም ዋስትና፤

ለ) የእዳ ሰነዱ ከገንዘብ አሰባሳቢው ሌሎች ዕዳዎች አንጻር ያለውን የክፍያ ቅደም ተከተል፤

ሐ) የገንዘብ አሰባሳቢውን ጠቅላላ ያልተከፈለ ዕዳና የዕዳ ክፍያ ግዴታዎቹን፤

መ) ግዴታን እንዳልተወጣ የሚያስቆጥሩ ሁኔታዎችንና የሚያስከትሉትን ውጤት፤ እና

ሠ) ዋናው ገንዘብ፣ ወለዱ ወይም ትርፋ ላይከፈል የሚችልበትን ስጋትና በክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ወይም በባለሥልጣኑ በኩል ምንም ዓይነት ዋስትና ያለመኖሩን የሚመለከት የተለየ የስጋት መግለጫ።

### 27. የተከለከሉ ሰነደ ሙዓለንዋዮች እና ሰነዶች

1/ ከሰው ወደ ሰው የሚደረግ የብድር ሰነዶች፣ በሃብት የተደገፉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እና ተዛማጅ ውሎች በክራውድ ፈንዲንግ መድረክ አማካኝነት መቅረብ አይችሉም።

2/ ባለሥልጣኑ የኢንቨስተሮችን ጥበቃ፣ የገበያውን ተዓማኒነት፤ ካፒታል መሰሰብን ለማስቻል እና የክራውድ ፈንዲንግ ገበያውን ልማት ለማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተጨማሪ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ምድቦችን ሊፈቅድ ወይም ሊከለክል ይችላል።

## 28. ከሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ ነፃ መሆን

በዚህ መመሪያ መሠረት በክራውድ ፈንዲንግ መድረክ አማካኝነት የወጡ ወይም የቀረቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በአዋጁ አንቀጽ 75(4)(ሠ) በተደነገገው መሰረት ከምዝገባ ነፃ ናቸው።

## 29. የሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱን ይፋ ማድረግ

1/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ተቃውሞ እንደሌለው ካሳወቀበት ወይም ተቃውሞውን እንዲያሳውቅ የተሰጠው የሃያ (20) ቀናት ጊዜ ካበቃ በኋላ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ የሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱን በክራውድ ፈንዲንግ መድረኩ አማካኝነት ለኢንቨስተሮች ተደራሽ ማድረግ አለበት።

2/ የአቅርቦት ሰነዱ ለኢንቨስተሮች ተደራሽ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ አሥራ አራት (14) ቀናት ሳያልፉ እና ሰነዱ ተደራሽ ከተደረገበት 30 ቀን በኋላ ሽያጩን መጀመር አይችልም።

3/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ የአቅርቦት ሰነዱን፣ የክራውድ ፈንዲንግ መድረኩ ውጪ በሌላ በማንኛውም የመገናኛ ዘዴ ተደራሽ ማድረግ አይችልም።

## 30. የአቅርቦት ክፍያዎች

1/ በክራውድ ፈንዲንግ ሽያጭ ለሚሳተፉ አካላት የሚከፈለው ጠቅላላ ክፍያ ከተሰበሰበው ጠቅላላ ገንዘብ ሁለት በመቶ (2%) መብለጥ የለበትም

2/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱትን የክፍያ ጣሪያዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ በጋይድላይን ሊያሻሽል ይችላል።

## 31. የአደራ ዝግ የባንክ ሒሳብ

1/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ሽያጭ ከመጀመሩ በፊት በቅድሚያ ከባለሥልጣኑ በሚሰጥ የጽሑፍ ትዕዛዝ መሠረት፣ በክራውድ ፈንዲንግ መድረኩ አማካኝነት ለሚካሄድ ለእያንዳንዱ የሽያጭ አቅርቦት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ በተሰጠው የንግድ ባንክ ውስጥ በገንዘብ አሰባሳቢው ስም የአደራ ዝግ የባንክ ሒሳብ እንዲከፈት ማድረግ አለበት።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ከሚካሄደው ሽያጭ አቅርቦት ጋር በተያያዘ በኢንቨስተሮች የተከፈለ ማንኛውም ገንዘብ ወደዚሁ የአደራ ዝግ የባንክ ሒሳብ ገቢ መደረግና መያዝ አለበት።

ምዕራፍ አምስት፡ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ማቅረቢያ ሰነድ ውስጥ መካተት ያለባቸው ዝቅተኛ ይፋ የማድረግ መስፈርቶች

## 32. የሽያጭ ማቅረቢያ ሰነድ ይዘቶች

1/ በክራውድ ፈንዲንግ ገንዘብ የሚሰበስብ ድርጅት የሚከተሉትን መራጃ የያዘ የአቅርቦት መግለጫ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡-

ሀ) ለምድብ አንድ ገንዘብ አሰባሳቢ፡-

I. የገንዘብ አሰባሳቢውንና የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙን ስም እንዲሁም ለሽያጭ የቀረበውን ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አይነት፣ ብዛት፣ ዋጋ፣ እና የሽያጭ ግዜ የሚገልጽ የፊት ገጽ፤

II. በቀረበው ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ላይ ኢንቨስት ማድረግ ስጋቶች ያሉበት መሆኑንና ኢንቨስት የማድረግ ማንኛውም ውሳኔ የስጋት ጉዳዮችን የሚመለከተውን ክፍል ጨምሮ የሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱን በማገናዘብ ላይ የተመሠረተ መሆን እንዳለበት ለኢንቨስተሮች የሚሰጥ ማስጠንቀቂያ፤

III. ስለ ገንዘብ አሰባሳቢው የሚሰጠው መረጃ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ) የገንዘብ አሰባሳቢው ሕጋዊና የንግድ ስም እንዲሁም የተመዘገበ አድራሻው፤

ለ) የገንዘብ አሰባሳቢው የተመሠረተበት ሀገር፣ የተመሠረተበት ቀንና የንግድ ምዝገባውን እና ያሉትን የንግድ  የሚመለከት መረጃ ጨምሮ ምስረታውን የሚመለከቱ ዝርዝሮች፤

ሐ) የገንዘብ አሰባሳቢው፣ የቁልፍ ኢንቨስተሮች፣ የቴክኒክ አጋሮች፣ የአደራጆች ዳይሬክተሮችና ከፍተኛ የኃላፊዎች፡

I. ስማቸው
II. ቋሚ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር ፣ ኢሚይል፣
III. ከዚህ በፊት የወንጀል ክስ ወይም የእምነት ማጉደል ጥፋተኝነት ብይን እንዳልተሰጠባቸው ማረጋገጫ፣

መ)ከገንዘብ አሰባሳቢው አክሲዮኖች ውስጥ ከ 5% በላይ የያዘ የእያንዳንዱ ሰው ስምና የድርሻ መጠን፤

ሠ) ከኢንቨስተሮችና ከባለሥልጣኑ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የተፈቀደለትን የገንዘብ አሰባሳቢው የግንኙነት ሰው የሚለይ መረጃ፤

ሰ) የንግድ ሥራው አጠቃላይ ገለጻ፤

ሸ) የገንዘብ አሰባሳቢውን ንግድ ለማካሄድ የሚያስፈልጉ ማናቸውም ፈቃዶች እና የተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሁንታዎችወይም ያልጸደቀ ከሆነ አሁን ያለበትን ደረጃ ፡፡

IV. ለሽያጭ ስለቀረቡት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የሚሰጥ መረጃ፡-

ሀ) ለሽያጭ የቀረቡት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ዓይነትና ክፍል መግለጫ፤

ለ) በገንዘብ ማሰባሰቢያው ሊሰበሰብ የታቀደው ከፍተኛው መጠን

መ) የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዙሩ የተሳካ ተደርጎ እንዲቆጠር መሰብሰብ ያለበት ዝቅተኛ መጠን ይሄውም ዝቅተኛ መጠን ሊሰበሰብ ከታቀደው ከፍተኛ መጠን 50% በታች መሆን አይችልም፡፡

ሠ) ለሽያጭ የቀረቡት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ዋጋ፤

ረ) የመክፈቻና የመዝጊያ ቀኖችን ጨምሮ የሽያጭ አቅርቦቱየግዜ ሰሌዳ፤

ሰ) የትርፍ ድርሻ ክፍያ፣ የድምፅ መስጠት፣ የቅድሚያ ግዢ፣ እና ተቋሙ በሚፈርስበት ጊዜ በሚቀረው ሀብት ላይ የመካፈል ድንጋጌዎችን ጨምሮ ከሰነደ-ሙዓለነዋዮቹ ጋር የተያያዙ መብቶች መግለጫ፤፤

ሸ) ገንዘብ አሰባሳቢው ከ ሽያጭ አቅርቦቱ በሚያገኘው ገቢ ለመደገፍ ያሰባቸው ዋና ዋና ተግባራት መግለጫ፤

ለ) ለምድብ ሁለት ገንዘብ አሰባሳቢ፣ ከላይ በ(ሀ) ሥር ከተመለከቱት መስፈርቶች በተጨማሪ የሚከተሉትን መረጃዎች ማቅረብ ይኖርበታል፡-

I. ገንዘብ አሰባሳቢው የሚያከናውነው ወይም ለማከናወን ያሰበው ንግድ ዝርዝር እና ሁሉን አቀፍ መግለጫ፣

II. ዋና ዋና የምርት ወይም የአገልግሎት ምድቦችን በመግለጽ የገንዘብ አሰባሳቢው አሠራርና ዋና ተግባራት መግለጫ፣

III. የገንዘብ አሰባሳቢው የንግድ ስትራቴጂና ዓላማዎች መግለጫ ከወደፊት ተግዳሮቶቹና ተስፋዎቹ ጋር በአንድነት፣

IV. ገንዘብ አሰባሳቢው የሚወዳደርባቸው ዋና ዋና ገበያዎች መግለጫ እንዲሁም ስለ ተወዳዳሪነት ደረጃው ለሚሰጣቸው መግለጫዎች መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣ እና

V. የአንድ አመት ኦዲት የተደረገ የሂሳብ መግለጫ፡፡

ሐ) ለምድብ ሦስት ገንዘብ አሰባሳቢ፣ ከላይ በ(ሀ) እና (ለ) ሥር ከተመለከቱት መስፈርቶች በተጨማሪ የሚከተሉትን መረጃዎች ማቅረብ ይኖርበታል፦

I. ገንዘብ አሰባሳቢው እስካሁን ያሳካቸው የንግድ እድገት ምዕራፎችና በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ለማሳካት የሚጠብቃቸው ምዕራፎች መግለጫ።

II. ግልጽና ወጥ የሆነ የንግድ ዕቅድ መግለጫ ።

III. ከገንዘብ ማሰባሰቡ ጋር የተያያዙ ወጪዎች መግለጫ።

IV. የገንዘብ አሰባሳቢውን የፋይናንስ ሁኔታ ወይም ደረጃ የሚገልጽ መረጃ፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፦

ሀ) በኢትዮጵያ የሒሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ በተቀመጠው ወቅታዊ የሒሳብ አያያዝ ደረጃ መሠረት የተዘጋጀ የሁለት ዓመታት ኦዲት የተደረገ የሒሳብ መግለጫ፤

ለ) የገንዘብ አሰባሳቢውን የፋይናንስ ሁኔታ የሚተነትን ዝርዝር ትንታኔ፤

ሐ) ያልተከፈሉ ዕዳዎች ዝርዝር፤

መ) ማናቸውንም ግምቶች ጨምሮ የ 3 ዓመታት የፋይናንስ ትንበያ።

V. የስጋት ጉዳዮች መግለጫ፤ ለገንዘብ አሰባሳቢው ወሳኝ የሆኑ የስጋት ጉዳዮች ከዋናው ጀምሮ በአስፈላጊነታቸው ቅደም ተከተል መቅረብ አለባቸው።

VI. ገንዘብ አሰባሳቢው እስካሁን ያገኘው የገንዘብ ድጋፍ ዝርዝር ካለ።

VII. በገንዘብ አሰባሳቢው ንግድ ወይም ፕሮጀክት ውስጥ የተሳተፉ የቴክኒክ አጋሮች ሚናና ኃላፊነት መግለጫ

VIII. በገንዘብ አሰባሳቢው ስም የተመዘገቡ አእምሮአዊ ንብረቶች፣ የንግድ ምልክቶች፤ የፈጠራ ባለቤትነት መብቶች፣ የቅጂ መብቶች ወይም የንግድ ምስጢሮች መግለጫ፤

IX. ለገንዘብ አሰባሳቢው አሠራር ወይም ለክራውድ ፈንዲንግ ሽያጭ አቅርቦቱ ጉልህ የሆኑ ማናቸውም የገንዘብ አሰባሳቢው ማናቸውም አይነት ውሎች፤

X. ገንዘብ አሰባሳቢውን የሚመለከቱ ማናቸውም ክሶች፣ የሕግ ሂደቶች ወይም የቁጥጥር ምርመራዎች ማጠቃለያ።

2/ በገንዘብ አሰባሳቢው ዳይሬክተሮች የተፈረመና የሚከተሉትን የሚገልጽ ማረጋገጫ፦

ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ሥር ለእያንዳንዱ ምድብ የተቀመጡትን የገንዘብ ማሰባሰቢያ ጣሪያዎችና በተለያዩ መድረኮች በተመሳሳይ ጊዜ የሽያጭ አቅርቦት ማቅረብ የተከለከለ መሆኑን የሚያውቁ መሆናቸውን፤

ለ) ገንዘብ አሰባሳቢው ከዚህ ሽያጭ አቅርቦት በፊት ባሉት አሥራ ሁለት (12) ወራት ውስጥ በክራውድ ፈንዲንግ አማካኝነት ያሰባሰበውን ማንኛውንም ገንዘብ፣ ይህ አቅርቦት በሚስተናገድበት የክራውድ ፈንዲንግ መድረክም ሆነ በሌላ በማንኛውም የክራውድ ፈንዲንግ መድረክ አማካኝነት የተሰበሰበውን ጨምሮ፣ እያንዳንዱን መድረክና በእርሱ ላይ የተሰበሰበውን መጠን በመለየት ይፋ ማድረጉን፤

ሐ) በዚህ ሽያጭ አቅርቦት ለመሰብሰብ የታሰበው መጠን በፊደል (ለ) ሥር ይፋ ከተደረጉት መጠኖች ጋር ተደምሮ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8(1) ሥር በምድቡ ላይ ተፈጻሚ የሆነውን ጣሪያ የማያልፍ መሆኑን፤ መ) በዚህ ሽያጭ አቅርቦት ለመሰብሰብ የታሰበው መጠን እንዲሁ ተደምሮ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8(2) ሥር የተደነገገውን የድምር ጣሪያ የማያልፍ መሆኑን፤ እና

ሠ) ገንዘብ አሰባሳቢው ሌላ የክራውድ ፈንዲንግ ሽያጭ አቅርቦት እያካሄደ ያልሆነ መሆኑንና ይህ አቅርቦት ክፍት ሆኖ እስካለ ድረስ ሌላ አቅርቦት የማይጀምር መሆኑን።

## 33. በሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱ ላይ የሚደረጉ ወሳኝ ለውጦች

1/ ገንዘብ አሰባሳቢው የሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱን ለክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ካስገባበት ቀን ጀምሮ ሽያጩ እስኪጠናቀቅበት ባለው ግዜ ውስጥ የሚከሰት ማንኛውንም ወሳኝ ለውጦች ለክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ እና ለሁሉም ኢንቨስተሮች ይፋ ማድረግ እና ሰነዱንም ማስተካል አለበት

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ዓላማ ወሳኝ ለውጥ የሚከተሉትን እና ለውጦች ያካትታል፦

ሀ) ለሽያጭ ከቀረቡት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ጋር የተያያዙ መብቶች፤

ለ) እንደ አግባብነቱ፤ የገንዘብ አሰባሳቢው የንግድ እና የፋይናንስ አቋም፣ ፤

ሐ) ከሽያጩ ገቢው አጠቃቀም፤

መ) ቁልፍ የአመራር ሠራተኞች፤

ሠ) የንግድ እንቅስቃሴው ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር ማንኛውም ወሳኝ ውል

ረ) የአንድን ኢንቨስተር ውሳኔ ሊነካ የሚችል ማንኛውም ጉዳይ።

3/ የአቅርቦት ጊዜው ከማብቃቱ በፊት ወሳኝ ለውጦች ሲከሰቱ፣ ኢንቨስተሮች ኢንቨስትመንታቸውን እንደገና እንዲገመግሙ እና የመሰረዝ መብታቸውን እንዲጠቀሙ ቢያንስ የአሥራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል።

# ምዕራፍ ስድስት ፤ የሽያጭ አቅርቦት ሂደትና ሥነ-ምግባር

## 34. በነባር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ የተጣለ የዝውውር ገደብ

1/ ከሽያጭ አቅርቦቱ በፊት በነባር ኢንቨስተሮች የተያዙ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ከሽያጭ አቅርቦቱ ቀን ጀምሮ ለሁለት (2) ዓመታት  የዝውውር ገደብ ይጣልባቸዋል።

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም፤ የዝውውር ገደቡ ከመጠናቀቁ በፊት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹን ማስተላለፍ የሚቻለው ዝውውሩ፦

ሀ) ለብቁ ኢንቨስተር፤ ወይም፤

ለ) በባለሥልጣኑ የተመዘገበ የሽያጭ አቅርቦት አካል ሆኖ፤

ሲከናወን ብቻ ነው።

## 35. የአቅርቦት ጊዜ

የአቅርቦት ጊዜው ከመቶ ሃያ (120) የካላንደር ቀናት መብለጥ የለበትም፤ ሆኖም በባለሥልጣኑ ይሁንታ ለተጨማሪ ሠላሳ (30) የካላንደር ቀናት ሊራዘም ይችላል።

## 36. የተደነገገው ዝቅተኛ የገንዘብ መጠን ገደብ

1/ የሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱ የሽያጭ አቅርቦቱ የተሳካ ተደርጎ እንዲቆጠር መሰብሰብ ያለበትን ዝቅተኛ መጠን ከታለመው መጠን አንጻር በምጣኔ ገልጾ ማስቀመጥ አለበት፤ ገንዘብ አሰባሳቢውም ይህንን ዝቅተኛ መጠን በአቅርቦት ጊዜው መጨረሻ ማሟላት አለበት።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ዝቅተኛ መጠን ሊሰበሰብ ከታሰበው ከፍተኛ መጠን ከሃምሳ በመቶ (50%) ማነስ የለበትም።

3/ ገንዘብ አሰባሳቢው በአቅርቦት ጊዜው መጨረሻ የተደነገገውን ዝቅተኛ መጠን ማሟላት ካልቻለ የሽያጭ አቅርቦቱ ይቋረጣል፤ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙም ይህንኑ ለባለስልጣኑ በማሳወቅ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 42 መሠረት ገንዘቡ ከአደራ ዝግ የባንክ ሒሳቡ ለኢንቨስተሮች ተመላሽ እንዲደረግ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ለባለስልጣኑ መጠይቅ አለበት።

4/ የሽያጭ አቅርቦት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት  ከተቋረጠ፣ ገንዘብ አሰባሳቢው  ለአዲስ የሽያጭ አቅርቦት ብቁ የሚሆነው አቅርቦቱ ከተቋረጠበት ቀን ጀምሮ [ስድስት (6) ወራት] ካለፉ በኋላ ብቻ ነው።

## 37. በገንዘብ አሰባሳቢው የሚወጣ ማስታወቂያ

1/ በገንዘብ አሰባሳቢው የሚወጣ ማስታወቂያ  በግልጽ ሊለይ የሚችል መሆን ያለበት ሲሆን፣ በውስጡ የያዘው መረጃም ትክክለኛ ያልሆኑ ወይም አሳሳች መሆን የሌለበት እና በሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱ ውስጥ ከተካተቱት መረጃዎች ጋር የተጣጣሙ መሆን አለባቸው።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ማስታወቂያ የሚከተሉትን ከያዘ አሳሳች ተደርጎ ይቆጠራል፡-

ሀ) ስለ ገንዘብ አሰባሳቢው የሥራ አፈጻጸም ወይም እንቅስቃሴዎች አስፈላጊውን ማብራሪያ ወይም ማስታወሻ ሳያካትት የገንዘብ አሰባሳቢውን አፈጻጸም የተጋነነ አድርጎ የሚያሳይ ከሆነ፤ ወይም

ለ) የገንዘብ አሰባሳቢውን የቀደመ አፈጻጸም በተሳሳተ መልኩ የሚስል ወይም የቀደሙ ትርፎች ወይም ገቢዎች ወደፊት እንደሚደገሙ በሚጠቁም መልኩ የሚያቀርብ ከሆነ።

3/ ማስታወቂያው ጥልቅ የቴክኒክና የሕግ ቃላትን ወይም ውስብስብ ቋንቋዎችን በስፋት መጠቀምንና የኢንቨስተሩን ትኩረት ሊያዘናጉ የሚችሉ ከመጠን ያለፉ ዝርዝሮችን ማስወገድ አለበት።

4/ ግልጽ ያልሆኑና የተጋነኑ ቃላትን መጠቀም የማይቻል ሲሆን፤ "ከፍተኛ የሽያጭ አቅርቦት"፣ "የላቀ የሽያጭ አቅርቦት"፣ "የፊካ መጨ ጊዜ"፣ "አስተማማኝ"፣ "ትርፋማ" እና መሰል ኢንቨስተሩን ሊያሳስቱ የሚችሉ  የተጋነኑ አባባሎችና አገላለጾችን መጠቀም የተከለከለ ነው።

5/ ማስታወቂያዎች ትርፍን ቃል የሚገቡ ወይም የሚያረጋግጡ መግለጫዎችን ወይም የምስክርነት ቃላትን መያዝ የለባቸውም።

6/ ማስታወቂያዎች ከሞዴሎች፣ ከዝነኞች፣ ከልብወለድ ገጸ-ባህርያት ወይም ከሥዕላዊ መግለጫዎች የሚሰጥ ድጋፍን መያዝ የለባቸውም።

7/ ማስታወቂያዎች ከፕሮግራሙ ጋር በተመሳሳይ ጊዜ በቴሌቪዥን ስክሪ ግርጌ ወይም በሌላ ሚዲያ ላይ በጠባብ መስመር ላይ በሚሰሩ ተንሸራታቾች መልክ መታየት የለባቸውም።

8/ ማስታወቂያ በሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱ ውስጥ ያሉ መረጃዎችን አመጣጥኖ ማቅረብ አለበት፤ ይህም የመረጃዎቹን አሉታዊና አወንታዊ ጎኖች ያለምንም ግድፈት ወይም መረጃዎችን መርጦ በማቅረብ ሳይሆን እኩል በሆነ ተደራሽነት ማቅረብን ያካትታል።

9/ የሚከተለው መግለጫ በሁሉም ዓይነት ማስታወቂያዎች ውስጥ በጉልህ መቀመጥ አለበት፡-

"እባክዎን የሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱን በሙሉ ያንብቡ፤ ምን ማድረግ እንዳለብዎት ግራ ከተጋቡም ለሽያጭ የቀረቡትን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለመግዛት ኢንቨስት ከማድረግዎ በፊት ፈቃድ ካለው አማካሪ ምክር ይጠይቁ።"

10/ ማስታወቂያው የሽያጭ አቅርቦቱን ጥንካሬ ወይም ድክመት ባለሥልጣኑ ወይም የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ እንዳጸደቀው፣ እንደፈቀደው ወይም እንዳረጋገጠው መግለጽ የለበትም።

11/ ከሽያጭ አቅርቦት ጋር በተያያዘ የገንዘብ አሰባሳቢው የሚያወጣው ማስታወቂያ አቅርቦቱ በሚስተናገድበት የክራውድ ፈንዲንግ መድረክ ላይ ብቻ መሆን አለበት፡፡

## 38. በክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ የሚወጣ ማስታወቂያ

1/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ ስለ ራሱ አገልግሎቶች ማስታወቂያ ማውጣት ና ኢንቨስተሮችን ወደ ክራውድ ፈንዲንግ መድረኩ መምራት ይችላል፡፡

2/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ በሚያቀርበው የክራውድ ፈንዲንግ መድረክ አማካኝነት ስለሚቀርቡ ማናቸውም የሽያጭ አቅርቦቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ማስተዋወቅ፣ ማስተዋወቂያ ሥራ መሥራት ወይም ማስታወቂያ ማውጣት አይችልም፡፡

## 39. በሽያጭ አቅርቦት ገጽ ላይ የሚቀመጡ ማስታወቂያዎች

1/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ በክራውድ ፈንዲንግ መድረኩ የሽያጭ አቅርቦቱ በሚገኝበት ገጽ ላይ የሚቀርበው ማንኛውም አቅርቦት በፍሬ ነገር ላይ የተመሠረተ፣ ወጥና ግልጽ በሆነ መልኩ መቅረቡን ማረጋገጥ አለበት፡፡

2/ የሽያጭ አቅርቦቱ ገጽ የሚከተለውን መግለጫ በግልጽና በጉልህ መያዝ አለበት፡-

"ይህ የሽያጭ አቅርቦት የቀረበው በገንዘብ አሰባሳቢው ነው፡፡ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ይህንን ኢንቨስትመንት አያስተዋውቅም ወይም አይመክርም፤ ለስኬቱም ምንም ኃላፊነት አይወስድም፡፡ ኢንቨስተሮች የራሳቸውን ገለልተኛ ግምገማ እንዲያደርጉ ይመከራሉ፡፡"

## 40. የኢንቨስተሮች ኢንቨስትመንትን የመሰረዝ መብት

1/ አንድ ኢንቨስተር በክራውድ ፈንዲንግ ሽያጭ አቅርቦት ላይ ኢንቨስት ለማድረግ የግዢ ቃል ኪዳን ካቀረበ በኋላ  የአርባ ስምንት (48) ሰዓታት የጥሞና ጊዜ ይኖረዋል፤ በዚህ ጊዜ ውስጥም ያለ ምንም ቅጣት ቃል ኪዳኑን መሰረዝ ይችላል፡፡ ይህ መብት ተፈጻሚ የሚሆነው የአቅርቦት ግዜው ያልተጠናቀቀ ከሆነ ነው

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም፣ በሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱ ላይ ወሳኝ ለውጥ ከተከሰተ ኢንቨስተሩ በአቅርቦት ጊዜው ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ያለ ምንም ቅጣት ከኢንቨስትመንቱ የመውጣት መብት ይኖረዋል፡፡

3/ ኢንቨስትመንታቸውን ለመሰረዝ የሚፈልጉ ኢንቨስተሮች በክራውድ ፈንዲንግ መድረኩ አማካኝነት የመሰረዝ ጥያቄ ማቅረብ አለባቸው፡፡

4/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ የመሰረዝ ጥያቄውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በሁለት (2) የሥራ ቀናት ውስጥ የመሰረዣውን ጥያቄ አግባብነት መወሰን አለበት፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ማረጋገጡን ሲያጠናቅቅ፣ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ ስለ መሰረዣው ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ በማሳወቅ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ ባለሥልጣኑ ትዕዛዝ እንዲሰጥ መጠየቅ አለበት።

6/ ባለሥልጣኑ ከክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ የገንዘብ ተመላሽ ጥያቄዎች ከተቀበለ በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ ለባንኩ የጽሑፍ ትዕዛዝ መስጠት አለበት።

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት ትዕዛዙ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በአምስት (5) የሥራ ቀናት ውስጥ ገንዘቡ ከአደራ ዝግ የባንክ ሒሳቡ በቀጥታ ወደ ኢንቨስተሩ ሒሳብ ተመላሽ መደረግ አለበት።

8/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ በአንድ የሽያጭ አቅርቦት ውስጥ የተረጋገጡ የገንዘብ ተመላሽ ጥያቄዎችን እንዲሁም የተፈጸሙ ተመላሾችን፣ የኢንቨስተሮችን ስሞች፣ መጠኖችና የሒሳብ መለያዎችን እንዲሁም የተመላሹን የጊዜ ማህተም ጨምሮ ዝርዝር መዝገብ መያዝ አለበት።

## 41. የሽያጭ አቅርቦትን ማገድ ወይም መሰረዝ

1/ ባለሥልጣኑ በራሱ ነሳሽነት ወይም በክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ አቅራቢነት የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲኖሩ የክራውድ ፈንዲንግ ሽያጭ አቅርቦትን ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል፡-

ሀ) በሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱ ወይም ለኢንቨስተሮች በተላለፉ መረጃዎች ውስጥ ማጭበርበር፣ የተሳሳተ አቀራረብ ወይም ወሳኝ መረጃዎችን አለመግለጽ ስለመኖሩ ምክኒያታዊ ጥርጣሬ የሚያስከትል ማስረጃ ሲኖር፤

ለ) ገንዘብ አሰባሳቢው የሚጠበቅበትን ሪፖርት ወይም የመረጃን ይፋ ማድረግን፣ የሒሳብ መግለጫ ወይም የወሳኝ ለውጥ ማስታወቂያ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ሳያቀርብ ከቀረ

ሐ) የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ የኢንቨስተሮችን ገንዘብ የመጠበቅ፣ ደንበኛህን ዕወቅ፣ የሕገወጥ የገንዘብ ዝውውርንና የሽብርተኝነት የገንዘብ ድጋፍን የመከላከል ግዴታዎችን ጨምሮ የኢንቨስተር ጥበቃ መስፈርቶችን ማሟላት ሳይችል ሲቀር፤

መ) ገንዘብ አሰባሳቢው ወይም የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች፣ አግባብነት ያላቸውን ሕጎች ወይም በሽያጭ አቅርቦቱ ውስጥ ይፋ የተደረጉትን ሁኔታዎች ሲጥስ፤

ሠ) የሽያጭ አቅርቦቱ መቀጠል ከሕዝብ ጥቅም፣ ከኢንቨስተርጥበቃ ወይም ከገበያ ተዓማኒነት ጋር የሚቃረን መሆኑን ባለሥልጣኑ ሲወስን፤ ወይም

ረ) ባለሥልጣኑ ተገቢ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸው ማናቸውም ሌሎች ምክንያታዊ ምክንያቶች ሲኖሩ።

2/ ባለሥልጣኑ የማገጃ ወይም የመሰረዣ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ለገንዘብ አሰባሳቢው በጽሑፍ ማስታወቂያ መስጠትና የመሰማት ዕድል መስጠት አለበት።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው ማስታወቂያ የሚከተሉትን መግለጽ አለበት፡-

ሀ) የታቀደው ማገድ ወይም መሰረዝ ምክንያቶች፤

ለ) ምላሽ ወይም የማስተካከያ እርምጃ ሊቀርብበት የሚችለው ጊዜ፤

ሐ) በግምገማው ወቅት የሚጣሉ ማናቸውም ጊዜያዊ ገደቦች።

4/ ጉዳዩ አፋጣኝ እርምጃ የሚጠይቅ ሲሆን፣ ገንዘብ አሰባሳቢውና የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ከእገዳው በኋላ ምላሽ የመስጠት ዕድል የሚሰጣቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባለሥልጣኑ ቅድመ ማስታወቂያ ሳይሰጥ የማገጃ ትዕዛዝ ሊያወጣ ይችላል።

## 42. በገንዘብ አሰባሳቢው በፈቃደኝነት የሚደረግ መሰረዝ

1/ ገንዘብ አሰባሳቢው የአቅርቦት ጊዜው ከማብቃቱ በፊት የመሰረዣ ማስታወቂያውን በጽሑፍ በማቅረብና የመሰረዣ ምክንያቱን በመግለጽ ለክራውድ ፈንዲንግ አገናኙና ለባለሥልጣኑ የሽያጭ አቅርቦቱ እንዲሰረዝ ሊጠይቅ ይችላል።

2/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ የመሰረዣ ማስታወቂያውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በአምስት (5) የሥራ ቀናት ውስጥ የሽያጭ አቅርቦቱን መሰረዝ አለበት።

## 43. ሽያጭን የማገድ ወይም የመሰረዝ ውጤት

1/ አንድ የሽያጭ አቅርቦት ሲታገድ ወይም ሲሰረዝ፡-

ሀ) የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ከሽያጭ አቅርቦቱ ጋር የተያያዘ ማንኛውንም ተጨማሪ የግዢ ቃል ኪዳን መሰብሰብ፣ ማስታወቂያ ማውጣት ወይም ኢንቨስተሮችን ማስገባት ወዲያውኑ ማቆም አለበት፤

ለ) መታገዱን ወይም መሰረዙን የሚገልጹ ማስታወቂያ እና ማስጠንቀቂያዎች በሽያጭ አቅርቦቱ ገጾች ላይ መውጣት አለባቸው፤

ሐ) በባለሥልጣኑ ካልተፈቀደ በስተቀር ምንም ዓይነት ድልድል፣ ዝውውር ወይም የገንዘብ ተመላሽ ሊፈጸም አይችልም፤

መ) የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ በሽያጭ አቅርቦቱ ላይ ለተሳተፉ ኢንቨስተሮች በሙሉ ስለ እግዱ ወይም መሰረዙ እና ስለ መብቶቻቸው ማሳወቅ አለበት።

2/ የሽያጭ አቅርቦቱ በሚሰረዝበት ጊዜ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ በአምስት (5) የሥራ ቀናት ውስጥ ባለስልጣኑ ለሽያጭ አቅርቦቱ የግዢ ቃል ኪዳን ለሰጡ ኢንቨስተሮች ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ ባንኩን እንዲያዝ በጽሑፍ መጠየቅ አለበት።

3/ ባለሥልጣኑ ከክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ የተረጋገጡትን የገንዘብ ተመላሽ ጥያቄዎች በተቀበለ በሁለት የስራ  ውስጥ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ ለባንኩ የጽሑፍ ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ትዕዛዙ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በአምስት (5) የሥራ ቀናት ውስጥ ገንዘቡ ከአደራ ዝግ የባንክ ሒሳቡ በቀጥታ ወደ ኢንቨስተሩ ሒሳብ ተመላሽ መደረግ አለበት፡፡

5/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ የደረሱትን የገንዘብ ይመለስልን ጥያቄዎችና የተፈጸሙ ተመላሾችን፣ የኢንቨስተሮችን ስምና የባንክ ሂሳብ ቁጥር፣ እንዲሁም ገንዘቡ መጠን እና ተመላሽ የተደረገበትን ትክክለኛ ቀን ና ሰዓት የያዘ ዝርዝር መዝገብ መያዝ አለበት፡፡

## 44. ከመሰረዝ በኋላ በሚቀርቡ ተከታይ የሽያጭ አቅርቦቶች ላይ የሚጣል ገደብ

በክራውድ ፈንዲንግ መድረክ አማካኝነት የቀረበ የሽያጭ አቅርቦት በባለሥልጣኑ ትዕዛዝ ወይም በገንዘብ አሰባሳቢው አማካኝነት ሲሰረዝ፣ ገንዘብ አሰባሳቢው አቅርቦቱ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ አስራ ሁለት (12) ወራት ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ባህርይ ያለው ተከታይ የሽያጭ አቅርቦት ለማቅረብ ብቁ አይሆንም፡፡

## 45. የድልድል ሂደት

1/ በሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱ ውስጥ በሌላ መልኩ ካልተገለጸ በስተቀር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በተመጣጣኝ ድርሻ መሠረት ይደለደላሉ፡፡

2/ ገንዘብ አሰባሳቢው የአቅርቦት ጊዜው ከተዘጋበት ቀን ጀምሮ በሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ውስጥ በሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱ ሁኔታዎች መሠረት ድልድሉን የማጠናቀቅና ውሳኔዎቹን ለክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡

3/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ የገንዘብ አሰባሳቢውን የመጨረሻ የድልድል ውሳኔ ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በአሥር (10) የሥራ ቀናት ውስጥ ድልድሉን በቴክኒካዊ ሥርዓቶቹ አማካኝነት መፈጸምና ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ ለኢንቨስተሮች በትክክል መሰራጨታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር ያለውን ኃላፊነት በሚወጣበት ጊዜ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ፦

ሀ) ማንኛውም ኢንቨስተር በዚህ መመሪያ የተደነገገውን የግል የኢንቨስትመንት ጣሪያ አለማለፉን ማረጋገጥ አለበት፤

ለ) የድልድል ማረጋገጫዎችን በመድረኩ አማካኝነት አዘጋጅቶ ለኢንቨስተሮች ማድረስ አለበት፤

ሐ) የኢንቨስተሮችን ማንነት፣ የግዢ ቃል ኪዳን መጠንና የተደለደሉላቸውን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ጨምሮ ሙሉና ትክክለኛ የኢንቨስተሮች መዝገብ አዘጋጅቶ ለገንዘብ አሰባሳቢውና ለባለሥልጣኑ ማስተላለፍ አለበት፡፡

## 46. የድልድል ሪፖርት

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 44(3) መሠረት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ድልድል ከተጠናቀቀ በኋላ ባሉት አምስት (5) የሥራ ቀናት ውስጥ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ የድልድል ሪፖርት አዘጋጅቶ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት።

2/ የድልድል ሪፖርቱ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

ሀ) የተደለደሉት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ጠቅላላ ብዛትና ለእያንዳንዱ ኢንቨስተር የተደለደለው መጠን፤

ለ) ለሽያጭ ከቀረበው ቁጥር በላይ ወይም በታች የግዢ ጥያቄ ስለመቅረቡ የሚገልጽ መግለጫ፤

ሐ) ለሽያጭ ከቀረበው ቁጥር በላይ የግዢ ጥያቄ ቀርቦ ከሆነ የተስተናገደበት መንገድ፤

መ) የድልድሉ ቀን።

3/ ገንዘብ አሰባሳቢውና የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ በድልድል ሪፖርቱ የቀረበው መረጃ እውነተኛ ስለመሆኑ በፊርማቸው ማረጋገጥ አለባቸው።

## 47. ከአደራ ዝግ የባንክ ሒሳብ ገንዘብ ስለመልቀቅ

የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ በአደራ ዝግ የባንክ ሒሳብ ውስጥ የተያዘው ገንዘብ ለገንዘብ አሰባሳቢው እንዲለቀቅ ማድረግ የሚችለው የሚከተሉት ሲሟሉ ነው፡-

ሀ) የአቅርቦት ጊዜው ሲጠናቀቅ፤

ለ) ለመሰብሰብ የታቀደው የገንዘብ መጠን የተገኘ እንደሆነ፤

ሐ) የአቅርቦት ጊዜው ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ አቅርቦት ጊዜው መጨረሻ ድረስ ከሽያጭ አቅርቦቱ ወይም ከገንዘብ አሰባሳቢው ጋር በተያያዘ ምንም ዓይነት ወሳኝ ለውጥ ያልተከሰተ ሲሆን፤ እና

መ) ገንዘቡ እንዲለቀቅ ባለሥልጣኑ ትዕዛዝ ሲሰጥ ነው።

## 48. ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ስለ ማውጣት

1/ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በገንዘብ አሰባሳቢው የሚወጡት የሽያጭ አቅርቦቱና የድልድል ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ መሆን አለበት።

2/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ የሚከተሉትን ማረጋገጥ አለበት፡-

ሀ) ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ በዲጂታል መልኩ መውጣታቸውን፤ እና

ለ) በኢንቨስተሩ ስም በአግባቡ መመዝገባቸውን።

3/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ የወጡትን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችና የባለቤቶቻቸውን መዝገቦች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 23 መሠረት የመያዝና የመጠበቅ እንዲሁም በአንቀጽ 24 መሠረት ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት።

## 49. ለክራውድ ፈንዲንግ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የግብይት አደረጃጀት

1/ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ከባለሥልጣኑ ቅድሚያ የጽሑፍ ይሁንታ በማግኘት፣ በክራውድ ፈንዲንግ መድረኩ አማካኝነት በመጀመሪያ ለሽያጭ የቀረቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለማዘዋወር የሚያስችል የግብይት አደረጃጀት ማንቀሳቀስ ይችላል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለባለስልጣኑ የሚቀርብ ማመልከቻ የግብይት አደረጃጀቱ የታቀዱ ደንቦች፣ የሥርዓቶቹንና የአሠራሩን መግለጫ፣ የክፍያ አወቃቀሩንና የጥቅም ግጭት አያያዝ ዝግጅቱን አካቶ መቅረብ አለበት።ከዚህ በተጨማሪም አስፈላጊ የሰው ሃይል እና ገንዘብ ሊኖረው

3/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ከባለስልጣኑ ይሁንታ ያገኘን የግብይት አደረጃጀት የሚያንቀሳቅስ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ፡-

ሀ) የዋጋ አወሳሰንን፣ የትዕዛዝ ማጣጣምና የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የባለቤትነት ለውጥ የሚደረግበት መንገድ፣ የሥራ ሰዓታትን፣ የተፈጸሙ ዝውውሮችን ይፋ ማድረግን እንዲሁም ዝውውሮችን በጊዜያዊነት ለማገድ የሚያስችሉ ምክንያቶችንና የአሰራር ሥነ-ሥርዓቶችን ጨምሮ በመገልገያው ላይ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ፍትሐዊና ሥርዓት ባለው መልኩ እንዲተላለፉ የሚያስችሉ የተጻፉ ደንቦችንና የአሰራር ሥነ-ሥርዓቶችን መያዝ አለበት፤

ለ) አደረጃጀቱ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ አለመሆኑን፣ የገንዘብ አከልነት ዋስትና እንደሌለውና በአስተላላፊው ወይም በተቀባዩ ላይ የሚጣሉ ክፍያዎችን፣ የአገልግሎት ክፍያዎችንና ወጪዎችን ጨምሮ የመገልገያውን ባህርይ በመድረኩ ላይ በጉልህ ይፋ ማድረግ አለበት፤

ሐ) ማንኛውም ግዥ ከመደረጉ በፊት በግዥው ለመሳተፍ ላቀደው ሰው በመጀመሪያው ሽያጭ አቅርቦት ወቅት ለኢንቨስተሮች የቀረበውን የሽያጭ ማቅረቢያ ሰነድና ተያያዥ ሰነዶች፣ በዚህ መመሪያ ምዕራፍ ሰባት መሠረት ይፋ የተደረጉ መረጃዎችን በሙሉ ተደራሽ ማድረግ አለበት፤

መ) ማንኛውም ዝውውር ከመፈጸሙ በፊት በግዥው ለመሳተፍ ያቀደው ሰው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 እና 16 መሠረት እንደ ኢንቨስተር መመዝገብና በአንቀጽ 18 ሥር የተመለከተውን የስጋት ማረጋገጫ ቅጽ ማስሞላት አለበት፤

ሠ) በአደረጃጀቱ በኩል የተገኘ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ሥር ከተደነገገው የኢንቨስትመንት ገደብ ጋር መቆጠሩን ማረጋገጥ አለበት፤

ረ) ግብይት የሚካሄድባቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የመጀመሪያ ደረጃ ሽያጫቸው በራሱ በክራውድ ፈንዲንግ መድረኩ በኩል የተፈጸመ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ብቻ መሆናቸውን ማረጋገጥ

አለበት፤ሰ) የተፈጸሙ ዝውውሮችን ብዛትና ዋጋ ጨምሮ በአንቀጽ 23 መሠረት መዝገብ መያዝና በአንቀጽ 24 መሠረት ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፤

ሸ) በአደረጃጀቱ ላይ በራሱ ሒሳብ መገበያየት፣ የገበያ ከፋች ሆኖ መሥራት ወይም ለግብይት ዓላማ ብድር መስጠት የለበትም፤ እና

ቀ) በአደረጃጀቱ ላይ ከሚገኙ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ጋር በተያያዘ የሚወጣ ማንኛውም ማስታወቂያ የዚህን መመሪያ አንቀጾች 36 እና 37 ማክበር አለበት።

4/ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ በአደረጃጀቱ ላይ ለዝውውር የሚቀርቡለት ገንዘብ አሰባሳቢ፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ በአደረጃጀቱ በሚቆዩበት ጊዜ ሁሉ በዚህ መመሪያ ምዕራፍ ሰባት ሥር ያሉትን ግዴታዎች ማክበር አለበት።

5/ በዚህ አንቀጽ ውስጥ የተመለከተው ማንኛውም ድንጋጌ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 33 ሥር፣ በገንዘብ አሰባሳቢው መመሥረቻ ሰነዶች ወይም በሌላ በማንኛውም አግባብነት ባለው ሕግ የተከለከለን ዝውውር እንደሚፈቅድ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም።

6/ ባለሥልጣኑ የኢንቨስተሮችን ጥቅም ለማስጠበቅ፣ ፍትሃዊና ሥርዓት ያለው ገበያን ለማረጋገጥ ወይም ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው፡ የአደረጃጀቱን እንቅስቃሴ ወይም በውስጡ የሚደረግ የማንኛውንም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት መመርመር፣ ማገድ ፣ ፍቃዱን መንጠቅ ይችላል።

7/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት ለሚንቀሳቀስ አደረጃጀት ተጨማሪ መስፈርቶችን የሚደነግጉ የአሠራር መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

### ምዕራፍ ሰባት ፤ መረጃን በቀጣይነት ይፋ የማድረግ ግዴታዎች

## 50. መስፈርቶች

1/ በክራውድ ፈንዲንግ መድረክ ላይ የተሳካ የሽያጭ አቅርቦት ያካሄደ ማንኛውም ገንዘብ አሰባሳቢ የሚከተሉትን ቀጣይነት ያላቸው የመረጃ ይፋ ማድረግ ግዴታ አለበት፡-

ሀ) በንግድ እንቅስቃሴው ላይ የሚከሰቱ ወሳኝ ለውጦች ለ) ዓመታዊ ኦዲት የተደረገ የሒሳብ ፤

ሐ) የሒሳብ መግለጫዎቹ ገንዘብ አሰባሳቢው ከሽያጭ አቅርቦቱ ያገኘውን ገቢ ትክክለኛ አጠቃቀም በበቂ ዝርዝር ይፋ ከሚያደርግ ሪፖርት ጋር አያይዞማቅረብ አለበት፤ እና

መ) ።

2/ ቀጣይነት ያላቸው የመረጃ ይፋ ማድረጊያዎች በአግባቡ የቀረቡ፣ አሳሳች ወይም አታላይ ያልሆኑ እንዲሁም ወሳኝ መረጃን ያላስቀሩ መሆን አለባቸው።

3/ በዚህ የመመሪያው ምዕራፍ ሥር የተመለከቱት መስፈርቶች ገንዘብ አሰባሳቢው፡-

ሀ) በባለሥልጣኑ የተመዘገበ የሕዝብ ኩባንያ እስኪሆን፤

ለ) ገንዘብ አሰባሳቢው ፈረሳውን ወይም ስረዛውን እስኪያጠናቅቅ፤ ወይም

ሐ) ገንዘብ አሰባሳቢው ያወጣቸውን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች መልሶ እስኪገዛ፣

ድረስ በእርሱ ላይ ተፈጻሚ ሆነው ይቀጥላሉ።

።

## 51. የሽያጭ ማቅረቢያና ቀጣይነት ያላቸው የመረጃ ይፋ ማድረጊያ ሰነዶች ተደራሽነት

1/ ቀጣይነት ያላቸው የመረጃ ይፋ ማድረጊያ ሰነዶች በሙሉ ለኢንቨስተሮች በክራውድ ፈንዲንግ መድረኩ፣ በገንዘብ አሰባሳቢው ድረ-ገጽ እንዲሁም ባለሥልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚወስናቸው ሌሎች መንገዶች መቅረብ አለባቸው።

2/ ገንዘብ አሰባሳቢው አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ማቅረብ ያለበትን መረጃዎች ለክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ እና ለኢንቨስተሮቹ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት። በተጨማሪም በድረ ገፁ ላይ በግልጽ በሚታይ መልኩ እና ቦታ ላይ ማስፈር አለበት።

3/ የክራውድ ፈንዲግ አገናኙ የተቀበለውን መረጃ በድረ ገፁ የገንዘብ አሰባሳቢውን መረጃዎች ይፋ በሚያደርግበት ገልጽ ላይ በግልጽ በሚታይ መልኩ እና ቦታ ላይ ማስፈር አለበት

## 52.መረጃ የማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳ

1) ገንዘብ አሰባሳቢው መረጃን በቀጣይነት የመቅረብ ግዴታ የገንዘብ አሰባሳቢው የበጀት አመት ባለቀ በ አንድ መቶ አምስት ቀን ውስጥ መከናወን አለበት ።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠባቀ ሆኖ የሚከተሉት ክስተቶች በተመለከተ ግን ገንዘብ አሰባሳቢው ክስተቶቹ ከተከሰቱ በ24 ሰዓታት ውስጥ ስለ እያንዳንዳቸው የሚገልጽ መረጃ ለእያንዳንዱ ኢንቨስተር በኢሜይል ተደራሽ ማድረግ፦

i. የገንዘብ አሰባሳቢው ንግድ መቋረጥ፤

ii. በገንዘብ አሰባሳቢው ንግድ ላይ የሚደረግ ለውጥ፤ ወይም

iii. የገንዘብ አሰባሳቢው ቁጥጥር መለወጥ

# ምዕራፍ ስምንት ፤ አስተዳደራዊ እርምጃዎችና ቅጣቶች

## 53. ያለ ፈቃድ የሚከናወኑ የክራውድ ፈንዲንግ ተግባራት

1/ ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖረው የክራውድ ፈንዲንግ መድረክ አገልግሎት መስጠት፣ ራሱን እንደ ክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ ማቅረብ ወይም በሌላ መልኩ የክራውድ ፈንዲንግ ተግባራትን ማከናወን አይችልም።

2/ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ድንጋጌ ሲጥስ፣ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች በተናጠል ወይም በጣምራ ሊወስድ ይችላል፡-

ሀ) ከብር 1,000,000 (አንድ ሚሊዮን) እስከ ብር 5,000,000 (አምስት ሚሊዮን) የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ፤

ለ) ያለ ፈቃድ የሚከናወነው ተግባር ወዲያውኑ እንዲቆምና ከኢንቨስተሮች የተሰበሰበው ገንዘብ በሙሉ ተመላሽ እንዲደረግ ማዘዝ፤ እና

ሐ) ድንጋጌውን የተላለፈውን ሰው እንዲሁም አግባብነት ያለው ሆኖ ሲገኝ ዳይሬክተሮቹንና ቁጥጥር ያላቸውን ባለአክሲዮኖቹን በጥቁር መዝገብ ውስጥ ማስፈር።

## 54. የማጭበርበር፣ የሸፍጥ ወይም አሳሳች ተግባር

1/ ማንኛውም ሰው ከክራውድ ፈንዲንግ ተግባር ጋር በተያያዘ እንደ ማጭበርበር ወይም ማታለል የሚቆጠር ማንኛውንም ድርጊት፣ አሠራር ወይም የንግድ ሂደት መፈጸም፣ ወሳኝ ፍሬ ነገርን በሚመለከት ሐሰተኛ መግለጫ መስጠት ወይም የተሰጡ መግለጫዎች አሳሳች እንዳይሆኑ የሚያስፈልግን ወሳኝ ፍሬ ነገር ማስቀረት የለበትም።

2/ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ድንጋጌ ሲጥስ፣ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች በተናጠል ወይም በጣምራ ሊወስድ ይችላል፡-

ሀ) ከብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) እስከ ብር 5,000,000 (አምስት ሚሊዮን) የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ፤

ለ) የግዢ ቃል ኪዳን የተሰጠበት ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ባለሥልጣኑ በሚወስነው የወለድ ምጣኔ ተጨምሮበት ለተጎዱ ኢንቨስተሮች ተመላሽ እንዲደረግ ማዘዝ፤ እና

ሐ) የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙን ፈቃድ ማገድ ወይም መሰረዝ፣ ወይም ገንዘብ አሰባሳቢውንና ኃላፊነት ያለባቸውን ዳይሬክተሮቹንና ቁጥጥር ያላቸውን ባለአክሲዮኖቹን ከማንኛውም የክራውድ ፈንዲንግ መድረክ በቋሚነት ማገድ፤

## 55. ከገንዘብ አሰባሳቢ ብቁነትና ምዝገባ ጋር የተያያዙ ጥሰቶች

1/ ገንዘብ አሰባሳቢው የሚከተሉትን ፈጽሞ ሲገኝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር ለተመለከቱት አስተዳደራዊ እርምጃዎች ተጠያቂ ይሆናል፡-

ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 መሠረት ብቁ ሳይሆን በክራውድ ፈንዲንግ መድረክ አማካኝነት ገንዘብ ሲያሰባስብ፤

ለ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 መሠረት በክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ በአግባቡ ሳይመዘገብ ገንዘብ ሲያሰባስብ፤

ሐ) የዚህን መመሪያ አንቀጽ 5(3) በመጣስ ቀደም ያለው የሽያጭ አቅርቦት በሂደት ላይ እያለ አዲስ የክራውድ ፈንዲንግ ሽያጭ አቅርቦት ሲጀምር፤ ወይም

መ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሠረት በምዝገባው ሂደት ሐሰተኛ፣ ትክክለኛ ያልሆነ፣ ያልተሟላ ወይም አሳሳች መረጃ ወይም ሰነድ ሲያቀርብ።

2/ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች በተናጠል ወይም በጣምራ ሊወስድ ይችላል፡-

ሀ) ከመስፈርቱ ውጪ በሆነው የሽያጭ አቅርቦት አማካኝነት ከተሰበሰበው ወይም ለመሰብሰብ ከታቀደው ጠቅላላ መጠን ከ 5% እስከ 15% የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ፤

ለ) ምዝገባውን ወይም የሽያጭ አቅርቦቱን መሰረዝ እንዲሁም የግዢ ቃል ኪዳን የተሰጠበት ገንዘብ ለኢንቨስተሮች ተመላሽ እንዲደረግ ማዘዝ፤

ሐ) ገንዘብ አሰባሳቢው ከአንድ (1) እስከ ሦስት (3) ዓመታት ባለው ጊዜ ውስጥ ወደ ማንኛውም የክራውድ ፈንዲንግ መድረክ እንዳይገባ ማገድ፤ እና

መ) ይፋዊ ወይም የግል ማስጠንቀቂያ መስጠት።

## 56. የገንዘብ ማሰባሰብ ላይ የተቀመጡ ጣሪያዎችን ማለፍ

1/ ማንኛውም ገንዘብ አሰባሳቢ በአንድ የሽያጭ አቅርቦትም ሆነ በሁሉም የክራውድ ፈንዲንግ መድረኮች በድምር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ሥር ከተመለከቱት ጣሪያዎች በላይ ገንዘብ ማሰባሰብ አይችልም።

2/ ገንዘብ አሰባሳቢው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ሥር የተመለከቱትን ጣሪያዎች እንዲያልፍ የፈቀደ፣ ያመቻቸ ወይም ጥሰቱን ለመለየትና ለመከላከል ያልቻለ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም 2 መሠረት ጥሰት ሲፈጸም ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች በተናጠል ወይም በጣምራ ሊወስድ ይችላል፡-

ሀ) በገንዘብ አሰባሳቢው ላይ፣ ተፈጻሚ ከሆነው ጣሪያ በላይ ከተሰበሰበው መጠን ከ 10% እስከ 20% የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ፤

ለ) በክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ላይ፣ ከብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ) እስከ ብር 2,000,000 (ሁለት ሚሊዮን) የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ፤

ሐ) ከጣሪያው በላይ የተሰበሰበውን መጠን ለኢንቨስተሮች በተመጣጣኝ ድርሻ ተመላሽ እንዲደረግ ማዘዝ፤

መ) ገንዘብ አሰባሳቢው ባለሥልጣኑ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ በማንኛውም የክራውድ ፈንዲንግ መድረክ ተጨማሪ ገንዘብ እንዳያሰባስብ ማገድ፤

ሠ) የክራውድፈንዲንግ አገናኙን ፈቃድ ማገድ ወይም መሰረዝ፣ ወይም የክራውድፈንዲንግ መድረኩን ሥራ ማገድ፤ እና

ረ) ይፋዊ ወይም የግል ማስጠንቀቂያ መስጠት።

## 57. የተሳሳተ አቀራረብና የተከለከለ ማስታወቂያ

1/ ማንኛውም ሰው ይህንን መመሪያ በሚጥስ መልኩ ማንኛውንም ማስታወቂያ፣ ሕትመት ወይም መግለጫ ማውጣት ወይም እንዲወጣ ማድረግ የለበትም፤ ይህም አሳሳች የሆነ፣ የተከለከለ አገላለጽ ወይም ድጋፍ የያዘ፣ ትርፍ ስለመኖሩ ቃል የሚገባ ወይም ማረጋገጫ የሚሰጥ፣ ወይም አቅርቦቱ ከሚስተናገድበት የክራውድ ፈንዲንግ መድረክ ውጪ የወጣ ማንኛውንም ማስታወቂያን ያካትታል።

2/ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ድንጋጌ ሲጥስ፣ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች በተናጠል ወይም በጣምራ ሊወስድ ይችላል፦

ሀ) ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) እስከ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ፤

ለ) ማስታወቂያው ወይም ሕትመቱ ወዲያውኑ እንዲነሳ፣ እንዲታረም ወይም እንዲሻር ማዘዝ፤

ሐ) ጥሰቱ የተደጋገመ ወይም ከባድ በሆነ ጊዜ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 41 መሠረት የሸያጭ አቅርቦቱን ማገድ ወይም መሰረዝ፤ እና

መ) ይፋዊ ወይም የግል ማስጠንቀቂያ መስጠት።

## 58. ወሳኝ ለውጥን ወይም ቀጣይነት ያላቸውን መረጃ ይፋ የማድረግ ግዴታዎችን አለመወጣት

1/ ገንዘብ አሰባሳቢው ወይም የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ የሚከተሉትን ሳይፈጽም ሲቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር ለተመለከቱት አስተዳደራዊ እርምጃዎች ተጠያቂ ይሆናል፦

ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 33 መሠረት በሽያጭ ማቅረቢያ ሰነዱ ላይ የተደረገን ወሳኝ ለውጥ ይፋ ማድረግ፤

ለ) በዚህ መመሪያ ምዕራፍ ሰባት ሥር የተመለከቱትን ቀጣይነት ያላቸው የመረጃ ይፋ ማድረግ መስፈርቶች ማክበር፤ ወይም

ሐ) ኦዲት የተደረገ የሒሳብ መግለጫን ጨምሮ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 50 ሥር የሚጠበቁትን ማስታወቂያዎች ወይም ሪፖርቶች በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ማቅረብ።

2/ ባለሥልጣኑ እንደ ጉዳዩ ክብደር እና ጥሰቱን በፈጸመው አካል ላይ በመመስረት የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች በተናጠል ወይም በጣምራ ሊወስድ ይችላል፡-

ሀ) ከብር 20,000 (ሃያ ሺህ) እስከ ብር 300,000 (ሦስት መቶ ሺህ) የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ፤ እንዲሁም ጥሰቱ ለቀጠለበት ለእያንዳንዱ ቀን ተጨማሪ ብር 2,000 (ሁለት ሺህ)፤

ለ) ያልቀረበው ይፋ መደረግ ያለበት መረጃ ወዲያውኑ ይፋ እንዲደረግ ማዘዝ፤

ሐ) ጥሰቱ እስኪታረም ድረስ ገንዘብ አሰባሳቢው የክራውድ ፈንዲንግ መድረኩን እንዳይጠቀም ማገድ፤

መ) የክራውድፈንዲንግ አገናኙን ፈቃድ ማገድ ወይም መሰረዝ፣ ወይም የክራውድፈንዲንግ መድረኩን ሥራ ማገድ፤ እና

ሠ) ይፋዊ ወይም የግል ማስጠንቀቂያ መስጠት።

## 59. የተገቢነት ቁመና ጥናት አለማካሄድ

1/ ገንዘብ አሰባሳቢን ከመመዝገቡ በፊት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 ሥር የሚጠበቅበትን የተገቢነት ቁመና ጥናት ያላካሄደ፣ ወይም በቂ የተገቢነት ቁመና ጥናት ሳያካሂድ በአንቀጽ 14 መሠረት ገንዘብ አሰባሳቢን የመዘገበ ወይም በአንቀጽ 15 መሠረት ለባለሥልጣኑ ማረጋገጫ ያቀረበ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር ለተመለከቱት አስተዳደራዊ እርምጃዎች ተጠያቂ ይሆናል።

2/ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን በተናጠል ወይም በጣምራ ሊወስድ ይችላል፡-

ሀ) ከብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ) እስከ ብር 2,000,000 (ሁለት ሚሊዮን) የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ፤

ለ) የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ በተመለከተው ገንዘብ አሰባሳቢ ላይ የተገቢነት ቁመና ጥናቱን እንዲያካሂድ ወይም በድጋሚ እንዲያካሂድ ማዘዝ፤

ሐ) ማስተካከያ እስኪደረግ ድረስ የተመለከተውን ገንዘብ አሰባሳቢ ምዝገባ ማገድ፤

መ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12(4)(ሐ) መሠረት የተሾመውን ዋና የተገቢነት ቁመና ጥናት ኃላፊ ከኃላፊነቱ ማንሳት ወይም ብቁ አለመሆኑን መወሰን፤ እና

ሠ) ጥሰቱ ከባድ፣ የተደጋገመ ወይም ሆን ተብሎ የተፈጸመ ሲሆን የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙን ፈቃድ ማገድ ወይም መሰረዝ።

## 60. ስጋትን ይፋ አለማድረግና የማስጠንቀቂያ መግለጫ አለማሳየት

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 መሠረት የስጋት ትምህርት ያልሰጠ፣ ስጋቶችን ይፋ ያላደረገ ወይም የማስጠንቀቂያ መግለጫን በጉልህ ያላሳየ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር ለተመለከቱት አስተዳደራዊ እርምጃዎች ተጠያቂ ይሆናል።

2/ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን በተናጠል ወይም በጣምራ ሊወስድ ይችላል፡-

ሀ) ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) እስከ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) የገንዘብ መቀጮ፤

ለ) የማስጠንቀቂያ መግለጫው ወይም የስጋት ይፋ ማድረጊያው ወዲያውኑ እንዲታይ ወይም እንዲታረም ማዘዝ፤

ሐ) መስፈርቱ እስኪሟላ ድረስ በመድረኩ ላይ አዳዲስ ኢንቨስተሮች እንዳይመዘገቡ ማገድ፤ እና

መ) ይፋዊ ወይም የግል ማስጠንቀቂያ መስጠት።

## 61. የስጋት ማረጋገጫ ቅጽ አለመቀበል

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 18 መሠረት በአግባቡ የተሞላ የስጋት ማረጋገጫ ቅጽ ሳይቀበል መደበኛ ኢንቨስተርን ለሽያጭ አቅርቦት የግዢ ቃል ኪዳን እንዲሰጥ የፈቀደ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር ለተመለከቱት አስተዳደራዊ እርምጃዎች ተጠያቂ ይሆናል።

2/ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን በተናጠል ወይም በጣምራ ሊወስድ ይችላል፡-

ሀ) ቅጹን በተገቢው ሁኔታ ባልሞላ በእያንዳንዱ ኢንቨስተር ብር 10,000 (አሥር ሺህ)፤

ለ) የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ያልቀረቡትን የስጋት ማረጋገጫ ቅጾች እንዲቀበል፣ ይህ ካልተቻለም የተመለከቱትን የግዢ ቃል ኪዳኖች እንዲሰርዝና ለኢንቨስተሮች ገንዘቡን ተመላሽ እንዲያደርግ ማዘዝ፤ እና

ሐ) መስፈርቱ እስኪሟላ ድረስ የሽያጭ አቅርቦቱን ማገድ።

## 62. በኢንቨስተሮች የሚፈጸሙ ጥሰቶች

1/ አንድ ኢንቨስተር የሚከተሉትን ሲፈጽም፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር ለተመለከቱት አስተዳደራዊ እርምጃዎች ተጠያቂ ይሆናል፡-

ሀ) በአንድ የሽያጭ አቅርቦትም ሆነ በሁሉም የክራውድ ፈንዲንግ መድረኮች በድምር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ሥር የተመለከቱትን የኢንቨስትመንት ጣሪያዎች ሲያልፍ፤ ወይም

ለ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 18 ሥር በሚሞላው የስጋት ማረጋገጫ ቅጽ ውስጥ ገቢውን ጨምሮ፣ ስለ ፋይናንስ አቅሙ ወይም ስለ ኢንቨስትመንት ጣሪያው ሐሰተኛ ወይም አሳሳች መግለጫ ሲሰጥ።

2/ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን በተናጠል ወይም በጣምራ ሊወስድ ይችላል፡-

ሀ) የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ ከጣሪያው በላይ የሆነውን ወይም ከመስፈርቱ ውጪ የተደረገውን ኢንቨስትመንት እንዲሰርዝና ከጣራ በላይ የሆነውን መጠን ለኢንቨስተሩ ተመላሽ እንዲያደርግ ማዘዝ፤

ለ) ባለሥልጣኑ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ የኢንቨስተሩን ሒሳብ ወይም ወደ ማንኛውም የክራውድ ፈንዲንግ መድረክ የመግባት መብቱን ማገድ፤ እና

ሐ) የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ጥሰት እያወቀ የፈቀደ ወይም ለመከላከል ምክንያታዊ እርምጃዎችን ያልወሰደ የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ በእያንዳንዱ ጥሰት ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) እስከ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) የገንዘብ መቀጮ ተጠያቂ ይሆናል።

## 63. ሌሎች ጥሰቶች

በዚህ ምዕራፍ በግልጽ ካልተደነገገ በስተቀር፣ ባለሥልጣኑ በዚህ ምዕራፍ ሥር ላልተመለከተ የዚህ መመሪያ ጥሰት፣ የጉዳዩን ሁኔታና ክብደት እንዲሁም ጥሰቱን የፈጸመውን ሰው ከግምት በማስገባት ከብር 10,000 (አሥር ሺህ) ያላነሰ የገንዘብ መቀጮ ሊጥል ይችላል።

## 64. ባለሥልጣኑ ምርመራ የማካሄድ ስልጣን

1/ ባለሥልጣኑ በማንኛውም የክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ፣ ገንዘብ አሰባሳቢ ወይም አግባብነት ባለው አገልግሎት ሰጪ ላይ ቅድመ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወይም ሳይሰጥ በቦታው በመገኘት ወይም ከቦታው ውጪ የሚደረግ ቁጥጥርና ምርመራ የማካሄድ እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን፣ መዝገቦችንና ሰነዶችን በሙሉ የማግኘት ስልጣን አለው።

2/ ባለሥልጣኑ በሚያካሂደው ምርመራ ወቅት የክራውድ ፈንዲንግ አገናኙ፣ ገንዘብ አሰባሳቢው እንዲሁም ማንኛውም ተያያዥ ወገንና አገልግሎት ሰጪ፣ እንዲሁም እያንዳንዱ ዳይሬክተር፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ሸሪክ፣ ጸሐፊ፣ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በእጃቸው የሚገኙትን አስፈላጊ መረጃዎች፣ መዝገቦች ወይም ሰነዶች የማቅረብ ግዴታ አለባቸው።

3/ ባለሥልጣኑ በምርመራው ሂደት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የውጭ ኦዲተሮችን፣ የሕግ አስከባሪ አካላትን ወይም አግባብነት ያላቸውን ሌሎች አካላትና ባለሙያዎችን ሊያሳትፍ ይችላል።

## ምዕራፍ ዘጠኝ ፤ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 65. ተጨማሪ መረጃ እና የተገቢነት ቁመና መስፈርቶች

1/ በዚህ መመሪያ የተደነገጉት መስፈርቶች አነስተኛ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ናቸው።

2/ የክራውድፈንዲንግ አገናኙ ባለሥልጣኑ በሚያጸድቀው የአሰራር ደንብ መሠረት የተገቢነት ቁመና መስፈርትን ለመወጣት፣ ስጋትን ለመገምገም፣ በቂ መረጃ ይፋ መደረጉን ለማረጋገጥ ወይም ፍትሃዊና ስርዓት የሰፈነበት ገበያን ለማስፈን አስፈላጊ የሆኑ ተጨማሪ መረጃዎችን፣ መግለጫዎችን ወይም መስፈርቶችን ከማንኛውም የሚመለከተው አካል እንዲቀርቡለት ወይም እንዲሟሉ ሊጠይቅ ወይም ሊጥል ይችላል።

### 66. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም ልማድ በዚህ መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

### 67. መመሪያው የሚጸናበት ቀን

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ከተመዘገበበትና በባለሥልጣኑ ይፋዊ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ፣ ____ ቀን ____ **2019** ዓ.ም

ሃና ተኸልቁ

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር